من معالم التوحيد

ከተውሒድ ዕርማቾች

إعداد: الشيخ عبدالرزاق بن عبدالمحسن البدر

ትርጉም፡ አቡ'ዓብዲልዓዚዝ/ዩሱፍ አሕመድ



http://t.me/alateriqilhaq

بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ

ምስጋና ሁሉ ለዓለማት ጌታ ለአሏህ - ሱብሃነሁ ወተዓላ - የተገባው ነው። ያማረ ፍጻሜ ደግሞ ለጥንቅቆቹ ነው። አላህ - ሱብሃነሁ ወተዓላ - ምንም ዓይነት ተጋሪና ከእርሱ በቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የሌለው መሆኑን ፤ ነብዩ ሙሀመድም ﷺ የአላህ አገልጋይና መልክተኛው መሆናቸውን በእርግጠኝነት እመሰክራለሁ።

የአላህ ውዳሴና ሰላምታ በነብዩ ሙሐመድ ﷺ፣ በቤተሰቦቻቸው እና በአጠቃላይ በባልደረቦቻቸው ላይ ይስፈን።

ከዚህ በመቀጠል፡

"ተውሒድ" የዲኑ መነሻም መድረሻም ፤ ውስጡም ውጩም ነው። ተውሒድ የመልእክተኞች ሁሉ የመጀመሪያም የመጨረሻም ጥሪ ነው። ተውሒድ **"ላኢላሃ ኢል'ላህ"** ለሚለው ቃል ትርጉም ነው። ለተውሒድ ሲባል ፍጥረታቶች ተፈጠሩ ፣ መልክተኞች ሁሉ ተላኩ ፣ መጽሓፎች ሁሉ እንዲወርዱ ተደረገ። በተውሒድ ምክንያት ሰዎች አማኝና ከሓዲ ፣ መልካምና ጠማማ ፣ የጀነትና የእሳት በሚል ከሁለት ተከፈሉ። ተውሒድ ለአካለ መጠን በደረሱ ሰዎች ላይ የመጀመሪያው ግዴታ ነው። ተውሒድ አላህ ከእርሱ ውጭ የማይቀበለው የሆነ ትክክለኛ የእስልምና እምነት ነው። ተውሒድ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ፣ ስለርሱ ማወቅና መተዋወስ ለእኛ በጣም አስፈላጊያችን የሆነ ጉዳይ ነው። በመሆኑም በዚህች "ሚን መዓሊሚ አት'ተውሒድ" በተባለች አጭር ኪታብ ውስጥ የሚከተሉትን አንኳር ነጥቦች መሰረት ያደረጉ የተውሒድ አርማዎችና ምልክቶች ማብራሪያ በዝርዝር ይገኛሉ።

ክፍል አንደኛ፡- የተውሒድ መለያዎችና ትሩፋቶች

ክፍል ሁለተኛ፡- የተውሒድ ትርጉምና እውነታ

ክፍል ሶስተኛ፡- ተውሒድን ማረጋገጥና ማሟላት

ክፍል አራተኛ፡- የተውሒድ አፍራሾችና አጉዳዮች

ክፍል አምስተኛ፡- የተውሒድ ምንጭና መነሻ

ክፍል ስድስተኛ፡- የተውሒድ ፍሬዎችና ፋይዳዎች

በዚህች አጭር ኪታብ የምንነጋገረው ከላይ በተጠቀሱት ስድስት አንኳር ነጥቦች ዙሪያ ይሆናል። እነዚህ አንኳር ነጥቦች በስፋት መብራራት የሚፈልጉ ሲሆኑ ነገር ግን በአላህ ፈቃድ የተፈለገውን አላማ በሚያሳካ መልኩ እጥር ምጥን አድርጌ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

እግዚአብሔር ከመጥፎው መንገድ ጠብቆ የመልካሙን መንገድ እንዲያመቻችልን አላህን - ሱብሃነሁ ወተዓላ - ብቻ እንማጸናለን።

ክፍል አንድ

የተውሒድ መለያዎችና ትሩፋቶች

ተውሒድ፡ ከፍተኛ ደረጃና ቦታ የሚሰጠው መሆኑን የሚጠቁሙ በርካታ መለያ ባህሪያትና ትሩፋቶች እንዳሉት እወቅ፡፡

ከእነርሱ መካከል አስሩን እንደሚከተለው እጠቁምሃለሁ፡፡

አንደኛ፡- የሚከተለው ቁርኣናዊ አንቀጽ እንደሚጠቁመው እኛ የተፈጠርንበት እና የተገኘንበት ዋና ዓላማ ለተውሒድና ተውሒድን ለማረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

﴿وَمَا خَلَقْتُ الْجِنَّ وَالْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ﴾

"ጅንና ሰውንም ኪግገዙኝ እንጅ ከኬካ (ዓካማ) አልፈጠርኳቸውም።" *(አዛ ዛሪያት፡ 56)*

"ኢልላ ሊየዕቡዱን" ፡ የሚለው የቁርኣን ቃል ትርጉም **"እኔን (በአምልኮት) ብቸኛ ኪያደርጉኝ"** ማለት ነው፡፡ በዚህ ዓለም የተፈጠርንበት ዋና ዓላማ ለቀልድና ለጨዋታ ሳይሆን ለተውሒድ ሲባል ነው፡፡ አላህ - ሱብሃነሁ ወተዓላ - ልቅ አድርጎ ሊተወን ሳይሆን እርሱን በብቸኝነት ልንገዛው ፈጠረን ፤ እርሱን በአምልኮ ብቸኛ ልናደርግ አስገኘን፡፡ የተውሒድ ሁኔታ ላቅ ያለ ለመሆኑ ከማስረጃ በኩል በዚህ ይብቃ፡፡

ሁለተኛ፡- ተውሒድ የነብያቶችና የሩሡሎች ጥሪ መሽከርከሪያ ምህዋር ነው፡፡ አላህ የላከው ማንኛውም ነብይ የጥሪው ትኩረትና መቆሚያ መሰረቱ ተውሒድ ነው፡፡ ለዚህም በርካታ ማስረጃዎች አሉ፡፡

አላህ በተከበሩት ቁርኣናዊ አንቀጾች የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَلَقَدْ بَعَثْنَا فِي كُلِّ أُمَّةٍ رَّسُولاً أَنِ اعْبُدُواْ اللّهَ وَاجْتَنِبُواْ الطَّاغُوتَ﴾

"በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ "አላህን ተገዙ ፤ ጣዖትንም ራቁ" በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል።" *(አን'ነሕል፡ 36)*

﴿ وَمَا أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ مِن رَّسُولٍ إِلَّا نُوحِي إِلَيْهِ أَنَّهُ لَا إِلَهَ إِلَّا أَنَا فَاعْبُدُونِ﴾

"ከአንተ በፊትም እነሆ ከእኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ በማለት ወደርሱ የምናወርድለት ቢሆን እንጅ ከመልክተኛ አንድንም አልላክንም።" *(አል'አንቢያእ፡ 25)*

﴿وَاسْأَلْ مَنْ أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ مِن رُّسُلِنَا أَجَعَلْنَا مِن دُونِ الرَّحْمَنِ آلِهَةً يُعْبَدُونَ﴾

"ከመልክተኞቻችንም ካንተ በፊት የላክናቸውን (ተከታዮቻቸውን) ከአልረህማን ሌላ የሚገዟቸው የሆኑን አማልክት አድርገን እንደሆነ ጠይቃቸው።" *(አዝ'ዙኽሩፍ፡ 45)*

﴿وَاذْكُرْ أَخَا عَادٍ إِذْ أَنذَرَ قَوْمَهُ بِالْأَحْقَافِ وَقَدْ خَلَتْ النُّذُرُ مِن بَيْنِ يَدَيْهِ وَمِنْ خَلْفِهِ أَلَّا تَعْبُدُوا إِلَّا اللَّهَ إِنِّي أَخَافُ عَلَيْكُمْ عَذَابَ يَوْمٍ عَظِيمٍ﴾

"የዓድንም ወንድም (ሁድን) ሕዝቦቹን በአሕቃፍ ባስጠነቀቀ ጊዜ አውሳካቸው። በስተፊቱና በስተኋላውም ብዙ አስፈራሪዎች በእርግጥ አልፈዋል። "ከአላህ በስተቀር አትግገዙ ፣ እኔ በእናንተ ላይ የከባድ ቀንን ቅጣት እፈራላችኋለሁና" በማለት (ባስጠነቀቀ ጊዜ)። *(አል'አህቃፍ፡ 21)*

"ኑዙር" ማለት መልክተኞች ማለት ነው። ከዚህ በፊት የነበሩትም ይሁን ወደኋላ የመጡት መልክተኞች "ከአላህ በቀር አትግገዙ" በሚለው አላማ ላይ አንድ ሆነዋል። ተውሒድ ፡ የነብያቶች እና የሩሡሎች ጥሪ መሰረት ነው። በዚህ ምክንያት ህዝቦቻቸው ከመልእክተኞች ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያደምጡት ቃል የተውሒድን ቃል ነው። ወደአላህ ጥሪ ሲያደርጉ አንድ ብለው የሚጀምሩት በተውሒድ ነው።

ምክንያቱም የኢስላም እምነት በእርሱ ላይ ነው የሚመሰረተው። የእምነቱ ምሳሌ ልክ እንደዛፍ ነው። ዛፍ መሰረትና ቅርንጫፎች እንዳሉት ይታወቃል። በመሰረቱ ላይ ካልሆነ በቀር ዛፉ ቀጥ ብሎ ሊቆም አይችልም። ዲኑም በመሰረቱ ላይ ካልሆነ ቀጥ ብሎ ሊቆም አይችልም። የዲን መሰረቱ ደግሞ ተውሒድ ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿أَلَمْ تَرَ كَيْفَ ضَرَبَ اللهُ مَثَلاً كَلِمَةً طَيِّبَةً كَشَجَرَةٍ طَيِّبَةٍ أَصْلُهَا ثَابِتٌ وَفَرْعُهَا فِي السَّمَاءِ﴾

"አካህ መልካምን ቃል ስሯ (በምድር ውስጥ) የተደላደለች ቅርንጫፏም ወደ ሰማይ (የረዘመች) እንደሆነች መልካም ዛፍ አድርጎ ምሳሌን እንዴት እንደገለጸ አላየኽምን?" *(ኢብራሒም: 24)*

ዛፍ ስሩ ሲቆረጥ እንደሚሞተው ሁሉ ፣ ዲንም በተውሒድ ላይ ካልቆመ ህይወት አይኖረውም። ሰዎችም በእርሱ ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም። ተውሒድ በዲኑ ውስጥ ያለው ቦታ ልክ የዛፉ ስር ለዛፉ መቆሚያ ፣ የቤት መሰረቱ ደግሞ ለህንጻው መቆሚያ እንደሚያገለግለው ማለት ነው።

ተውሒድ፡ የነብያቶችና የሩሡሎች ጥሪ ዋናው መሽከርከሪያ ፣ የመልእክታቸው ትኩረት እንደሆነ ከሚጠቁሙ መረጃዎች መካከል የሚከተለው የነብዩ ﷺ ትክክለኛ ሐዲስ ይገኛል፡-

"ألأنبياء إخوة من علات ، وأمهاتهم شتى ، ودينهم واحد"

"ነብያቶች ከአንድ አባት ፣ ከተለያዩ እናቶች የሆኑ ወንድማማቾች ናቸው። ዲናቸው አንድ ነው።" (ሙስሊም፡ 2365)

በአባት አንድ ናቸው ማለት በተውሒድ አንድ ናቸው ፣ ሁሉም በተመሳሳይ ወደአላህ ተውሒድ ነው ጥሪ የሚያደርጉት ማለት ነው። እናቶቻቸው የተለያዩ ናቸው ማለት ደግሞ ህግና መመሪያቸው የተለያዩ ናቸው ማለት ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿لِكُلٍّ جَعَلْنَا مِنكُمْ شِرْعَةً وَمِنْهَاجًا﴾

"ከእናንተ ከሁሉም ህግንና መንገድን አደረግን።" (አል'ማኢዳህ፡ 48)

ሶስተኛ፡- ተውሒድ ለአካለ መጠን በደረሱ ሰዎች ላይ የመጀመሪያው ግዴታ መሆኑ ነው። ወደዚህ እምነት ለመግባት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው መጀመሪያ ግዴታ የሚሆንበት ተውሒድ ነው። ወደአላህ ጥሪ ማድረግ የፈለገ ማንኛውም ሰው ጥሪው የሚጀምረው በተውሒድ ነው። ይህን የሚጠቁሙ በርካታ መረጃዎች አሉ። ከእነርሱ መካከል የሚከተለው የረሡል ﷺ ሐዲስ ይገኝበታል፡-

"أمرت أن أقاتل الناس حتى يشهدوا أن لا إله إلا الله"

“ከአላህ በቀር በአውነት የሚመለክ አምላክ የለም ብለው አስኪመሰክሩ ድረስ ሰዎችን ልጋደል ታዝዣለሁ።” (ቡኻሪ፡ 25, ሙስሊም፡ 22)

ሌላው መረጃ ሙዓዝ ﷺ ወደየመን ሲላክ ረሡል ﷺ ያስተላለፉት መልእክት ነው።

"إنك تقدم على قوم أهل كتاب ، فليكن أول ما تدعوهم إليه عبادة الله" الحديث .

“ወደመጽሐፍ ባለቤቶች ትላደለህ። የመጀመሪያው ጥሪህ የአላህ ዒባዳ (አምልኮ) ይሁን።” (ቡኻሪ፡ 1458, ሙስሊም፡ 19)

በሌላ ዘገባ፡ -

"إنك تقدم على قوم من أهل الكتاب ، فليكن أول ما تدعوهم إلى أن يوحدوا الله تعالى"

“ወደመጽሐፍ ባለቤቶች ትላደለህ። የመጀመሪያው ጥሪህ አላህን (በአምልኮ) ብቸኛ አንዲያደርጉ ይሁን።” (ቡኻሪ፡ 7372)

በሌላ ዘገባ፡ -

"إنك ستأتي قوما أهل الكتاب ، فإذا جئتهم ، فادعهم إلى أن يشهدوا أن لا إله إلا الله ، وأن محمدا رسول الله"

“ወደመጽሐፍ ባለቤቶች ትላደለህ ፤ ያገኘሀቸው ጊዜ ከአላህ በቀር በአውነት የሚመለክ አምላክ የሌለ መሆኑን ፤ ሙሀመድም የአላህ መልክተኛ መሆናቸውን አንዲመሰክሩ ጥሪ አድርግላቸው።” (ቡኻሪ፡ 1496, ሙስሊም፡ 19)

ተውሒድ፡ ለአላህ መጠን በደረሱ ሰዎች ላይ የመጀመሪያው ግዴታ ነው። ሰዎች ወደዚህ ዲን መጀመሪያ የሚገቡት በእርሱ ነው። የዲኑ መሰረት ተውሒድ ነው ፤ ዲኑ በእርሱ ላይ ይቆማል ፤ በእርሱም ላይ ይጀመራል።

አራተኛው፡- ሰላም ለማግኘትም ይሁን በሁለቱ አገር ወደቅኑ ጎዳና ለመመራት ምክንያቱ ተውሒድ ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿الَّذِينَ آمَنُواْ وَلَمْ يَلْبِسُواْ إِيمَانَهُم بِظُلْمٍ أُوْلَئِكَ لَهُمُ الأَمْنُ وَهُم مُّهْتَدُونَ﴾

"እነዚያ ያመኑና እምነታቸውን በበደል ያልቀላቀሉ እነዚያ ከእነርሱ ጸጥታ አላቸው። እነሱም የተመሩ ናቸው።" *(አል'አንዓም፡ 82)*

ጸጥታ ወይም ሰላም በአላህ እጅ ነው። አላህ - ሱብሃነሁ ወተዓላ - ዲኑን ፍጹም ለእርሱ ብቻ ለሚያጠሩ የተውሒድ ሰዎች እንጂ ጸጥታን ለማንም አይሰጥም።

ከዚህ በላይ የጠቀስነው የቁርኣን አንቀጽ በወረደ ጊዜ ሶሃቦች -ረዲየሏሁ ዓንሁም- በጣም ተጨነቁ። ወደረሡል ﷺ በመምጣት የሚከተለውን ጥያቄ አቀረቡ፡-

"يا رسول الله ! أينا لم يظلم نفسه؟"

"የአላህ መልክተኛ ሆይ! ማንኛችን ነን ነፍሳችንን የማንበድለው?"

ይህ ማለት "ከእኛ መካከል አንድም ሰው አይኖርም ፤ ነፍሱን የሚበድል ቢሆን እንጂ" ማለታቸው ነው።

ወይም "እያንዳንዳችን ነፍሳችንን እንበድላለን በመሆኑም ከጸጥታም ይሁን ከመመራት ምንም አይነት ድርሻ አይኖረንም" ማለታቸው ነው።

ከዚያም ነብዩ ﷺ የሚከተለውን ምላሽ ሰጡ፡-

"ليس ذاك"

"ነገሩ አንደዚያ (አናንተ አንደተገነዘባችሁት) አይደለም"

"በቁርአን አንቀጹ ላይ የተጠቀሰው በደል ፣ አናንተ የተገነዘባችሁት ግይነት በደል አይደለም።" "የዚያ ጥበበኛና ደግ የሆነው ባሪያ - ሉቅማን - የተናገረውን ንግግር አላነበባችሁምን?" አሏቸው።

﴿إِنَّ الشِّرْكَ لَظُلْمٌ عَظِيمٌ﴾

"ሚጋራት ታላቅ በደል ነውና" ያለውን (አስታውስ)" (ሉቅማን፡ 13)

በዚህ አንቀጽ የሚገኘውን "ዙልም" ሽርክ ወይም ማጋራት በሚለው የአላህ መልክተኛ ﷺ ተርጉመውታል። (ቡኻሪ፡6937)

ይህ የቁርአን አንቀጽ ምንም ሳያጋራ በአላህ ያመነ ሰው በሁለቱም አገር ጸጥታና መመራት እንዳለው ይጠቁመናል። የተውሒድ ሰው ከሆነ በሁለቱም አገር አላህ ጸጥታን እና መመራትን ይሰጠዋል። ይህ ደግሞ የተውሒድ ልዩ ገጽታው ነው።

አምስተኛው፡- በሌሎች እምነቶች ተቃራኒ እርስ በርስ ከመጋጨትና ከመዋዠቅ ነጻ የሆነ እምነት ነው።

ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው ቁርኣናዊ አንቀጽ ነው፡-

﴿وَلَوْ كَانَ مِنْ عِندِ غَيْرِ اللهِ لَوَجَدُواْ فِيهِ اخْتِلاَفًا كَثِيراً﴾

"ከአላህ ሌላ ዘንድ በነበረ ኖሮ በርሱ ውስጥ ብዙን መከያየት ባገኙ ነበር።" (አን'ኒሳእ፡82)

ሰዎች በሚፈጥሯቸው እምነቶች ውስጥ በአብዛኛው እርስ በርስ የሚጣረሱና የሚምታቱ ነገሮች ይገኙበታል።

ከአላህ ኪታብና ከረሡል ﷺ ሱና የመነጨ ትክክለኛና ጥልቅ የሆነ እምነት ፣ ሰላማዊ የሆነ ዓቂዳ ከሆነ ግን ከዚህ ሁሉ ነጻ ነው።

ስድሥተኛ፡- ተውሒድ ከሰላማዊ ተፈጥሮ ፣ ከተስተካከለ አቅል ጋር ተስማሚ ነው። ተውሒድ የተፈጥሮ እምነት ነው። የሰው ልጅ በተፈጥሮ እምነቱ ላይ ቢተው ከተውሒድ ውጭ ሌላን አይቀበልም። ምክንያቱም አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ እንደተናገረው ፣ ተውሒድ ከተፈጥሮ ጋር የሚስማማ የሰው ልጅ የተፈጠረበት እምነት ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿فَأَقِمْ وَجْهَكَ لِلدِّينِ حَنِيفًا فِطْرَةَ اللَّهِ الَّتِي فَطَرَ النَّاسَ عَلَيْهَا لَا تَبْدِيلَ لِخَلْقِ اللَّهِ ذَلِكَ الدِّينُ الْقَيِّمُ وَلَكِنَّ أَكْثَرَ النَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ﴾

"ወደአውነት ተዘንባይ ሆነህም ፊትህን ከሃይማኖት ቀጥ አድርግ። የአላህን ፍጥረት ያችን አላህ ሰዎችን በእርሷ ላይ የፈጠረባትን (ሃይማኖት ያዟት) ። የአላህን ፍጥረት መለወጥ የለም። ይህ ቀጥተኛ ሃይማኖት ነው። ግን አብዛኛዎቹ ሰዎች አያውቁም።" (ሩሮ፡ 30)

ሽርክ (ማጋራት) ደግሞ ከተፈጥሮው መውጣትና ማዘንበል ነው።

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲሰል - ቁድስ አላህ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

"وإني خلقت عبادي حنفاء كلهم ، وإنهم أتتهم الشياطين فاجتالتهم عن دينهم"

"እኔ ባሮቸን ሁሉ በቀጥተኛው መንገድ ላይ ፈጠርኳቸው። ሰይጣናት ወደነርሱ በመምጣት ከዲናቸው አንዲዘነበሉ አደረጓቸው።" (ሙስሊም፡ 2865)

"ኽለቅቱ ሚባዪ ሁኳፉ" ማለት የተፈጥሮ እምነት በሆነው ተውሒድ ላይ ሰዎችን ፈጠርኳቸው ማለት ነው።

"ፈአተትሁም አሸሸያጢን ፈጅታከትሁም" ማለት ደግሞ ከዲናቸው ወይም ከተውሒዳቸው እንዲዘነበሉ አደረጓቸው ማለት ነው።

በትክክለኛ ዘገባ አቡሁረይራ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፈዋል፡-

"ما من مولود إلا يولد على الفطرة ، فأبواه يهودانه ، وينصرانه كما تنتجون البهيمة ، هل تجدون فيها من جدعاء ، حتي تكونوا أنتم تجدعونها؟"

وفي رواية: **"فأبواه يهودانه ، أو ينصرانه ، أو يمجسانه ، كما تنتج البهيمة بهيمة جمعاء ، هل تحسون فيها من جدعاء؟"**

"አንድም የሚወለድ የለም በተፈጥሮው (አምነት ላይ ቢሆን) አንጅ ፤ ወላጆቹ አይሁድ ያደርጉታል ፣ ክርስቲያን ያደርጉታል። አንስሳት ስትወለድ አናንተ ካልቆረጣችኋት በቀር ከሰውነት አካኳ የተቆረጠ አካል ታገኛላችሁ?" *(ቡኻሪ፡ 6599)*

በሌላ ዘገባ፡ **"ወላጆች አይሁድ ያደርጉታል ወይም ክርስቲያን ያደርጉታል ወይም መጁስ ያደርጉታል። አንስሳት ምንም አንሰን የሌላት ልጅ ትወልዳለች። ከልጇ አካል ላይ ቆራጣ ታገኛላችሁን?"** *(ቡኻሪ፡ 1359, ሙስሊም፡ 2658)*

አንዲት እንስሳት ከእናቷ ሆድ ጆሮዋና ጣቶቿ የተሟሉ ሆነው ትወለዳለች። እግሯ ወይም እጇ ወይም ጆሮዋ ወይም የመሳሰሉት አካሎቿ ከተቆረጠ ይህ ተፈጥሯዊ አይደለም። ይህ በተሟላ ሁኔታ ከተወለደች በኋላ ሰዎች የሚያደርጉት ነው። የአላህ መልክተኛ ﷺ **"አናንተ አስከምትቆርጧት ድረስ"** በማለት ተናግረዋል።

ልክ እንደዚሁ የሰው ልጅ በተፈጥሮ እምነቱ ላይ ነው የሚወለደው። ክርስቲያን ወይም አይሁድ ወይም መጂስ ወይም በተለያዩ የጥመት አመለካከቶች ተበክሎ ብናገኘው በወላጆች ወይም በአደገበት አካባቢ ተጽእኖ የተፈጠረ ችግር እንጅ የተፈጥሮ እምነቱ አይደለም።

وينشأ ناشئ الفتيان منا على ما كان عوده أبوه

ወጣቶቻችን ያድጋሉ ታዳጊ ሆነው (በአካባቢው ባህሪ) አባቱ ባስለመደው

قال ﷺ: "فأبواه يهودانه ، أو ينصرانه ، أو يمجسانه" ولم يقل : "أو يسلمانه"

የአላህ መልክተኛ ﷺ *"ወላጆቹ ሙስሊም ያደርጉታል"* የሚል ሳይሆን "ወላጆቹ አይሁድ ወይም ክርስቲያን ወይም መጂስ ያደርጉታል" የሚል ቃል ነው የተናገሩት።

ምክንያቱም ያደገው የተወለደው በተፈጥሮ እምነቱ ላይ ነው። ተውሒድ የተፈጥሮ ሐይማኖት ነው። ሽርክ ወይም ማጋራት ፣ ጥመትና ከንቱ አመለካከት ደግሞ የተፈጥሮ እምነትን የሚጋጭ ከተውሒድ ጋር የማይገናኝ ነው። ተውሒድ ከተስተካከለ ከአዕምሮ ጋር ይስማማል። ያልተጣመመ ፣ ያልተዘነበለ አዕምሮ ከተውሂድ ውጭ ሌላን አይወድም ፤ ተውሒድን እንጅ አይቀበልም። ከእርሱ ዘንድ ሰላማዊ አዕምሮ ኖሮት ማን ነው በርካታ አማልክትን የሚወድ ! ማን ነው ወደ ቁባና የአፈር አምልኮት የሚያዘነብለው !

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿يَا صَاحِبَيِ السِّجْنِ أَأَرْبَابٌ مُّتَفَرِّقُونَ خَيْرٌ أَمِ اللهُ الْوَاحِدُ الْقَهَّارُ۞مَا تَعْبُدُونَ مِن دُونِهِ إِلاَّ أَسْمَاء سَمَّيْتُمُوهَا أَنتُمْ وَآبَآؤُكُم مَّا أَنزَلَ اللهُ بِهَا مِن سُلْطَانٍ﴾

“የተለያዩ አምላኮች ይሻላሉን? ወይስ አሸናፊው አንዱ አላህ? “ከእርሱ ሌላ እናንተና አባቶቻችሁ (አማልክት ብላችሁ) የጠራችኋቸውን ስሞች እንጅ አትገዝዙም። አላህ በእርሷ ምንም አስረጅ አላወረደም።” (ዩሱፍ፡ 39-40)

ዘይድ ብን ዓምር ብን ኑፈይል የተባለው የጃሂልያው የተውሒድ ሰው ከአካባቢው ማህበረሰብ በእምነት በተለየ ጊዜ የሚከተለውን ግጥም ገጥሟል፡-

أربا واحدا أم ألف رب أدين إذا تقسمت الأمور

عزلت اللات والعزى جميعا كذلك يفعل الجلد الصبور

فلا عزى أدين ولا ابنتيها ولا صنمي بني عمرو أدير

አንድ ወይስ አንድ ሽ ጌታ የተለያዩ ጉዳዮች ሲገጥሙኝ የማምነው (የማታ ማታ)

ከዑዛም ከላት ከሁሉም ተለየሁ ልክ እንደዚሁ ይሰራል ታጋሹ ብልሁ

ዑዛን እስከ ሁለት ልጆቿ በፍጹም አላመልክም ወደበኒ ዓምር ሁለት ጣዖቶች ፊቴንም አላዞርም

ዘይድ ብን ዓምር ብን ኑፈይል ፡ “ፍየልን የፈጠረ ፣ እርሷ የምትጠጣውን ውሃ ከሰማይ ያወረደ ፣ እርሷ የምትመገበውን አትክልት ከምድር ያበቀለ አላህ ሆኖ እያለ እርሷን ስታርዱ ከአላህ ስም ውጭ እንዴት ታነሳላችሁ?” በማለት አላህን በማላቅ ፤ ጣዖታትን ዝቅ በማድረግ የመካ ቁረይሾችን እርድ ያነውር ነበር። *(ቡኻሪ ፡ 3826)*

ዓለምን የፈጠረ የሆነው አላህ ከነውርና ከጉድለት የጸዳ ፣ ሙሉ የሆነ ባህሪ ያለው ፣ ተናንሰን እና ተዋርደን ልንገዛው የሚገባ መሆኑን ከማወቅ የበለጠ ለአዕምሮ ግልጽና የተብራራ አንድም ነገር የለም።

መልክተኞች የመጡት ይህን ጉዳይ ለማሳወቅና ለመዘርዘር ነው። የተውሒድ ውበቱና የሸርክ አስቀያሚነቱ በአዕምሮና በተፈጥሮ የተረጋገጠ ህያው የሆነ ልቦና ፣ ሰላማዊ የሆነ ዓቅልና ትክክለኛ የሆነ ተፈጥሮ ካለው ሰው ዘንድ በጣም ግልጽ የሆነና የታወቀ ጉዳይ ነው።

ሰባተኛው፡- በዚህ ዓለምም ይሁን በወዲያኛው ዓለም በዘውታሪነትና በቀጣይነት በትክክል የሚያስተሳስር እርሱ ብቻ ነው። እንደተውሒድ በሰው ልጆች መካከል እርስ በርስ የሚያስተሳስር አንድም ነገር የለም። ምክንያቱም ተውሒድ በኢማን ባለቤቶች መካከል በዚህ ዓለምም ይሁን በወዲያኛው ዓለም ቀሪ ፣ ቀጣይነት ያለውና ዘላለማዊ የሆነ የማስተሳሰሪያ ገመድ ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿الْأَخِلَّاءُ يَوْمَئِذٍ بَعْضُهُمْ لِبَعْضٍ عَدُوٌّ إِلَّا الْمُتَّقِينَ﴾

"ወዳጆች በዚያ ቀን ከፊላቸው ከከፊሉ ጠላት ነው። አላህን ፈሪዎች ብቻ ሲቀሩ።" *(አዝ ዙኽሩፍ፡ 67)*

﴿وَتَقَطَّعَتْ بِهِمُ الْأَسْبَابُ﴾

"በእነርሱ መካከል ምክንያቶች በተቆረጡ ጊዜ (የሚሆኑትን ባወቁ ኖሮ በተጸጸቱ ነበር)።" *(አል'በቀራህ፡ 166)*

ይህ ማለት በመካከላቸው የነበረው ትስስር በተቋረጠ ጊዜ ማለት ነው።

በተውሒድ እና በኢማን የተመሰረተ ግንኙነት እና ውዴታ ካልሆነ በቀር ማንኛውም ግንኙነት ይቆራረጣል ፤ በመካከል ያለው ፍቅር ይወገዳል።

ለአላህ የሆነው የትስስር ገመድ ይዘወትራል ፣ ግንኙነቱ የተቀጠለ ይሆናል። በሌላ አላማ ላይ የተመሰረተ የትስስር ገመድ ይቆራረጣል ፤ ይለያያል። ግንኙነቱ የፈለገው ጠንካራና ጥልቅ ቢመስል እንኳ ፣ በተውሒድ ወይም ባማረ ኢማን የተመሰረተ ካልሆነ በቀር በዚህ ምድራዊ ዓለምም ወይም በወዲያኛው ዓለም መቋረጡ አይቀርም። የተውሒድ ውዴታ ግን በዚህ ምድራዊ ዓለምም ይሁን በወዲያኛው ዓለም ቀጣይነትና ዘውታሪነት አለው።

ስምንተኛው፡- የተውሒድ ምንጭ ሰላማዊ ነው። ተውሒድ የተቀዳው ከጥሩና ከጣፋጭ ምንጭ ነው። እርሱም ከአላህ ኪታብና ከልብ ወለዳቸው ከማይናገሩት ረሡል ﷺ ሱና የተቀዳ ነው።

ዘጠነኛው፡- ተውሒድ ጽኑ እንዲሁም ጥብቅ ነው። ተውሒድን ወይም ዲኑን እስከትንሳኤ ቀን ድረስ በጽናት ሊያቆየውና ሊጠብቀው አላህ ዋስትና ወስዷል።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿هُوَ الَّذِي أَرْسَلَ رَسُولَهُ بِالْهُدَى وَدِينِ الْحَقِّ لِيُظْهِرَهُ عَلَى الدِّينِ كُلِّهِ وَلَوْ كَرِهَ الْمُشْرِكُونَ﴾

"እርሱ ያ አጋሪዎቹ ቢጠሉም መልክተኛውን (ሙሐመድን) በቅን መንገድና በእውነተኛ ሐይማኖት ላይ ከሃይማኖቱ ሁሉ በላይ ይፋ ያደርገው ዘንድ የላከው ነው።" *(አት-ተውባህ፡ 33)*

﴿إِنَّ اللَّهَ يُدَافِعُ عَنِ الَّذِينَ آمَنُوا﴾

"አላህ ከእነዚያ ካመኑት ላይ ይከላከልላቸዋል።" *(ሐጅ፡ 38)*

﴿يُثَبِّتُ اللَّهُ الَّذِينَ آمَنُواْ بِالْقَوْلِ الثَّابِتِ فِي الْحَيَاةِ الدُّنْيَا وَفِي الآخِرَةِ﴾

“አካሀ እነዚያን ያመኑትን በቅርቢቱም ሕይወት በመጨረሻይቱም (በመቃብር) በተረጋገጠው ቃል ያረጋቸዋል።” (ኢብራሒም፡ 27)

አሥረኛው፡ ተውሒድ በርካታ ፍሬዎችንና ትሩፋቶችን የሰበሰበ ነው። በዚህ ዓለምም ይሁን በወዲያኛው ዓለም የተለያዩ መልካም አሻራዎች አሉት።

ሁለተኛው አንኳር ነጥብ

የተውሒድ ምንነትና እውነታ

ተውሒድ፡ “ወሐደ” (አንድ አደረገ) ፣ “ዩወሒዱ” (አንድ ያደርጋል) ለሚሉት ግሶች ስርወ ቃል ነው። ተውሒድ ነጠላን የሚጠቁም ስርወ ቃል ነው። የአላህ ተውሒድ አላህን በአምልኮ ብቸኛ ማድረግ ፣ እርሱ በሚለይባቸው ነገሮች ሌሎችን አካላት ከእርሱ ላይ ማጋራትን ማራቆት ማለት ነው። አላህ - ሱብሃነሁ ወተዓላ - እርሱ በሚለይባቸው ነገሮችም ይሁን ባሮች ለእርሱ ተፈጻሚ በሚያደርጓቸው ሐቆቹ በአንዳችም ነገር ለእርሱ ሸሪካ የለውም።

ሩቡቡያ - ማለት በዚህ ዓለም የማስተናበር ፣ የመግደል ፣ ህይዎት የመስጠት ፣ የመመገብ ፣ የመፍጠርና ነገሮችን እንደፈለገ የማገለባበጥ ስልጣን ያለው አላህ መሆኑን ማረጋገጥ ማለት ነው። ይህም የአላህ ልዩ መገለጫ ነው።

በመልካም ስሞቹ ፣ በከፍተኛ መገለጫዎቹ ፣ ተፈጻሚ በሆኑ እቅዶቹ ፣ አጠቃላይ በሆነው ችሎታው ፣ ሰፊ በሆነው እውቀቱ በእነዚህ ስሞቹና መገለጫዎቹ ሁሉ ሙሉ መሆኑ አላህ የሚለይባቸው ናቸው። ከእነዚህ አላህ ከሚለይባቸው መገለጫዎች አንዱን አሳልፎ ለፍጡራን የሰጠ ይህን የተውሒድ ክፍል አፍርሶታል።

ባሮች በፈጣሪያቸው ላይ ያለባቸው ሐቆች በእርሱ ላይ አንድም ሳያጋሩ እርሱን ብቻ ሊያመልኩት ነው።

كما في حديث معاذ رضي الله عنه ، قال له النبي ﷺ: "يا معاذ ، تدري ما حق الله على العباد؟ وما حق العباد على الله؟ قال: قلت : الله ورسوله أعلم؟

قال: "فإن حق الله على العباد أن يعبدوا الله ، ولا يشركوا به شيئا ، وحق العباد على الله أن لا يعذب من لا يشرك به شيئا"

የአላህ መልክተኛ ﷺ ለሙዓዝ رضي الله عنه የሚከተለውን ጥያቄ ጠይቀውታል፡-

“ሙዓዝ ሆይ! በባሮች ላይ ያለውን የአላህ ሀቅ ታውቃለህን? በአላህ ላይ ያለውን የባሮች ሐቅ ታውቃለህን?” እርሱም፡ “አላህና የአላህ መልክተኛ አዋቂ ናቸው” በማለት ምላሽ ሰጠ። ረሡል ﷺ፡ “በባሮች ላይ ያለው የአላህ ሐቅ በእርሱ አንድም ሳያጋሩ አላህን ብቻ ኪገዙ ነው ፤ በአላህ ላይ ያለው የባሮች ሐቅ ደግሞ በእርሱ ምንም ያላጋሩትን ላይቀጣቸው ነው” በማለት ምላሽ ሰጡ። *(ቡኻሪ፡ 5967, ሙስሊም፡ 30)*

አምልኮ የአላህ ሐቅ ነው። ከአምልኮ አንድንም አሳልፎ ለሌላ የሰጠ ተውሒዱን አፈረሰ።

ተውሒድ፡ ማለት እርሱ በሚለይባቸውና በሐቆቹ አላህን ብቸኛ ማድረግ ማለት ነው።

ሽርክ፡ ማለት ከአሏህ ሐቆች ወይም እርሱ በሚለይባቸው ነገሮች አላህን ከሌሎች አካላት ጋር ማስተካከል ማለት ነው።

የተውሒድ እውነታ፡ ማንንም ሳናጋራ አላህን በአምልኮት መነጠል ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጹ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَاعْبُدُواْ اللّهَ وَلاَ تُشْرِكُواْ بِهِ شَيْئًا﴾

“አካህንም ተገዙ ። በእርሱም ምንንም አታጋሩ።” *(አን’ኒሳእ፡ 36)*

﴿وَقَضَى رَبُّكَ أَلاَّ تَعْبُدُواْ إِلاَّ إِيَّاهُ﴾

“ጌታህም (እንዲህ ሲል) አዘዘ፡- እርሱን እንጅ ሌላን አትገዙ።” (አል’ኢስራእ፡23)

﴿وَمَا أُمِرُوا إِلَّا لِيَعْبُدُوا اللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ﴾

“አላህን ሃይማኖትን ከእርሱ ብቻ አጥሪዎች፣ (እንጅ ያልታዘዙ ሲሆኑ) (አል’በይናህ፡5)

በዚህም ተውሒድ በሶስት እንደሚከፈል ግልጽ ይሆናል ማለት ነው። እነርሱም ተውሒድ አር ' ሩቡብያ ፣ ተውሒድ አስማዕ ወስ ' ሲፋት እና ተውሒድ አል ' ኡሉሒያ ናቸው።

<u>አንደኛው ተውሒድ አር ' ሩቡብያ፡</u> አላህ በመፍጠርም ፣ ሲሳይ በመስጠትም ፣ ሁሉን ተቆጣጣሪ በመሆኑም ፣ ጸጋን በመስጠቱና ሁሉን በማገለባበጡ ብቸኛ መሆኑንና በእነዚህ ነገሮች ምንም አይነት ተጋሪ የሌለው መሆኑን አምኖ ብቸኛ ማድረግ ማለት ነው። አላህ በተከበረው ቁርአናዊ አንቀጾቹ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿قُلْ مَن رَّبُّ السَّمَاوَاتِ وَالأَرْضِ قُلِ اللهُ﴾

“የሰማያትና የምድር ጌታ ማን ነው?” በላቸው። “አላህ ነው” በል። (አር’ረዕድ፡16)

﴿قُل لِّمَنِ الْأَرْضُ وَمَن فِيهَا إِن كُنتُمْ تَعْلَمُونَ۝سَيَقُولُونَ لِلَّهِ قُلْ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ۝ قُلْ مَن رَّبُّ السَّمَاوَاتِ السَّبْعِ وَرَبُّ الْعَرْشِ الْعَظِيمِ۝سَيَقُولُونَ لِلَّهِ قُلْ أَفَلَا تَتَّقُونَ۝قُلْ مَن بِيَدِهِ مَلَكُوتُ كُلِّ شَيْءٍ وَهُوَ يُجِيرُ وَلَا يُجَارُ عَلَيْهِ إِن كُنتُمْ تَعْلَمُونَ﴾

“ምድርና በውስጧ ያለው ሁሉ የማን ነው? የምታውቁ ብትሆኑ (ንገሩኝ)” በላቸው። “በእርግጥ የአላህ ነው” ይሉሃል። “ታዲያ አትገሰጹምን?” በላቸው። “የሰባቱ ሰማያት ጌታና የታላቁ ዐርሽ ጌታ ማን ነው?” በላቸው። “በእርግጥ አላህ ነው” ይሉሃል። “እንግዲያ አትፈሩትምን?” በላቸው። “የነገሩ ሁሉ ግዛት በእጁ የሆነ እርሱ የሚጠብቅ በእርሱ ላይ የሚይጠበቅ ማን ነው?

የምታውቁ እንደሆናችሁ (መልሱልኝ) በላቸው። (አል'ሙእሚኑን፡ 84-88)

﴿ذَلِكُمُ اللَّهُ رَبُّكُمْ فَتَبَارَكَ اللَّهُ رَبُّ الْعَالَمِينَ﴾

"ይሄችሁ ጌታችሁ አላህ ነው። የዓለማትም ጌታ አላህ ላቀ።" (ጋፊር፡ 64)

ሁለተኛው ክፍል፡ ተውሒዱል አስማኢ ወስ'ሲፋት በቁርኣን በሐዲስ በመጡ መልካም ስሞቹና ከፍተኛ የሆኑ መገለጫዎች አላህን ብቸኛ ማድረግ ማለት ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጾቹ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿اللَّهُ لَا إِلَهَ إِلَّا هُوَ لَهُ الْأَسْمَاء الْحُسْنَى﴾

"አላህ ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም። ከእርሱ መልካሞች የሆኑ ስሞች አሉት።"
(ጦሃ፡ 8)

﴿قُلِ ادْعُواْ اللّهَ أَوِ ادْعُواْ الرَّحْمَنَ أَيًّا مَّا تَدْعُواْ فَلَهُ الأَسْمَاء الْحُسْنَى﴾

"አላህን ጥሩ ወይም አር'ረሕማንን ጥሩ ፤ (ከሁለቱ) ማንኛውንም ብትጠሩ (መልካም ነው)። ከእርሱ መልካም ስሞች አሉትና" (አል'ኢስራእ፡ 110)

﴿هُوَ اللَّهُ الَّذِي لَا إِلَهَ إِلَّا هُوَ عَالِمُ الْغَيْبِ وَالشَّهَادَةِ هُوَ الرَّحْمَنُ الرَّحِيمُ۞ هُوَ اللَّهُ الَّذِي لَا إِلَهَ إِلَّا هُوَ الْمَلِكُ الْقُدُّوسُ السَّلَامُ الْمُؤْمِنُ الْمُهَيْمِنُ الْعَزِيزُ الْجَبَّارُ الْمُتَكَبِّرُ سُبْحَانَ اللَّهِ عَمَّا يُشْرِكُونَ۞هُوَ اللَّهُ الْخَالِقُ الْبَارِئُ الْمُصَوِّرُ لَهُ الْأَسْمَاء الْحُسْنَى يُسَبِّحُ لَهُ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَهُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ﴾

"እርሱ አላህ ነው ፤ ያ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ ፤ ሩቁንና ቅርቡን ዐዋቂ የሆነ ነው። እርሱ እጅግ በጣም ርህሩህ በጣም አዛኝ ነው። እርሱ አላህ ነው። ያ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ ፤ ንጉሱ ከጉድለት ሁሉ የጠራው ፣ የሰላም ባለቤቱ ፣ ጸጥታን ሰጭው ፣ ባሮቹን ጠባቂው ፣ አሸናፊው ፣ ሃያሉ ፣ ኩሩው ነው።

አላህ ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ። እርሱ አላህ ፈጣሪው (ከኢምንት) አስገኚው ፣ ቅርጽን አሳማሪው ነው። ከእርሱ መልካሞች ስሞች አሉት። በሰማያትና በምድርም ያለው ሁሉ ከእርሱ ያሞግሳል። እርሱም አሸናፊና ጥበበኛም ነው።"

(ሐሸር፡ 22-24)

ሶስተኛው ክፍል፡ ተውሒድ አል'ኡሉሒያ አላህን በአምልኮት ፣ በዱዓ ፣ ተስፋ በማድረግ ፣ በፍርሀት ፣ በስለት ፣ በእርድ ፣ በሶላት ፣ በጾም እና በመሳሰሉ አምልኮቶች አላህን ብቸኛ ማድረግ ማለት ነው። ዲንን ለእርሱ ብቻ ማጥራትና ከማጋራት መጽዳት ማለት ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَمَا أُمِرُوا إِلَّا لِيَعْبُدُوا اللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ﴾

"አላህን ሃይማኖትን ከእርሱ ብቻ አጥሪዎች፣ (እንጅ ያልታዘዙ ሲሆኑ) *(በይናህ፡ 5)*

﴿أَلَا لِلَّهِ الدِّينُ الْخَالِصُ﴾

"ንቁ! ፍጹም ጥሩ የሆነው ሃይማኖት የአላህ ብቻ ነው።" *(አዝ ዙመር፡ 3)*

﴿قُلْ إِنَّ صَلَاتِي وَنُسُكِي وَمَحْيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ۞لَا شَرِيكَ لَهُ وَبِذَلِكَ أُمِرْتُ وَأَنَا أَوَّلُ الْمُسْلِمِينَ﴾

"ስግደቴ ፣ እርደም ፣ ሕይወቴም ፣ ሞቴም ከአለማት ጌታ ከአላህ ነው" በል። "ከእርሱ ተጋሪ የለውም። በዚህም (በማጥራት) ታዘዝኩ።" *(አል'አንዓም፡ 162-163)*

የአላህ መልክተኛ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡-

"من مات وهو يدعو من دون الله ندا دخل النار"

"ከአላህ ውጭ ማኦትን አየጠራ የሞተ ሰው አሳት ገባ።" (ቡኻሪ፡ 4497) ተውሒድና የተውሒድ እውነታ ማለት ይህ ነው። ለእነዚህ የተውሒድ ክፍሎች ሁሉ የራሳቸው የሆኑ ተቃራኒዎች አሏቸው።

((**ተውሒድ አር'ሩቡቢያ** ፡ ማለት አላህ ብቸኛው ፈጣሪ ፣ መጋቢ ፣ ህይዎት ሰጪ ፣ ገዳይ ፣ ሁሉንም ነገር የሚያስተናብር ፣ ፍጡራኑን ሁሉ እንደፈለገ የሚያገላብጥ ፣ ፍጡራኖችን በመቆጣጠር አንድም ተጋሪ የሌለው መሆኑን ካረጋገጥክና ካወቅህ ፣ የዚህ ተቃራኒ አንድ ባሪያ አላህ እንጅ ማንም በማይችለው ነገር ከአላህ ጋር ሌሎች አካላት ይህን ዓለም እንደፈለጉ የሚያንቀሳቅሱ አሉ ብሎ ማመኑ ነው።

ተውሒድ አስማኢ ወስ'ሲፋት ፡ ማለት አላህ እራሱን በጠራበት ስም መጥራት ፣ ራሱ በገለጸው መገለጫ መግለጽ ፣ እንዲሁም ነብዩ ሙሀመድ ﷺ ከእርሱ ላይ ማመሳሰልን በማራቅት አላህን በገለጹበት መግለጽ መሆኑን ካረጋገጥክና ካወቅህ የዚህ ተቃራኒ ሁለት ነገሮች ይኖራሉ። እነዚህን ሁለት ነገሮች "ኢልሀድ" የሚለው ስያሜ ያጠቃልላቸዋል።

<u>አንደኛ፡-</u> በቁርኣንና በሱና የተረጋገጠውን ሙሉና የተላቀ የሆነውን የአላህ ባህሪያት ማራቅት ነው።

<u>ሁለተኛ፡-</u> የአላህን መገለጫዎች ከፍጡራን መገለጫዎች ጋር ማመሳሰል ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጾች የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿لَيْسَ كَمِثْلِهِ شَيْءٌ وَهُوَ السَّمِيعُ البَصِيرُ﴾

"የሚመስለው ምንም ነገር የለም። እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው።" (አሸ'ሹራ፡ 11)

﴿قُلِ ادْعُواْ اللّهَ أَوِ ادْعُواْ الرَّحْمَنَ أَيًّا مَّا تَدْعُواْ فَلَهُ الأَسْمَاء الْحُسْنَى﴾

"አላህን ጥሩ ወይም አር'ረሕማንን ጥሩ ፤ (ከሁለቱ) ማንኛውንም ብትጠሩ (መልካም ነው) ። ከእርሱ መልካም ስሞች አሉትና" *(አል'ኢስራእ፡ 110)*

ተውሒድ አል'ኡሉሒያ ፡ በማንኛውም የአምልኮ አይነቶች አላህን ብቸኛ ማድረግ ፤ ከአላህ ውጭ ከሚገኙ አካላት ላይ አምልኮትን ማራቆት መሆኑን ካወቅህ የዚህ ተቃራኒው ከአምልኮ አይነቶች አንዱን ቆርሶ ከአላህ ውጭ ለሚገኙ አካላት አሳልፎ መስጠት ነው። ይህ ከአብዛኛው ሙሽሪኮች ዘንድ የሚገኝ ሲሆን በመልእክተኛችና በህዝቦቻቸው መካከል የነበረው ውዝግብም በዚህ የተውሒድ ክፍል መሆኑ ይታወቃል።)) *(መዓሪጀል ቀቡል 1/418)*

ሶስተኛው አንኳር ነጥብ

ተውሒድን ማረጋገጥና ማሟላት

ተውሒድን ማረጋገጥ ከፍተኛና የላቀ ደረጃ አለው። ረሡል ﷺ በታወቀው ሐዲሳቸው የተውሒድ ባለቤቶች ያለምንም ሒሳብ እና ቅጣት ጀነት እንደሚገቡ አውስተዋል።

وعن ابن عباس وغيره رضي الله عنهم قال صلى الله عليه وسلم : "معهم سبعون ألفا يدخلون الجنة بغير حساب ولا عذاب" ثم ذكرهم بقوله : "هم الذين لا يسترقون ، ولا يتطيرون ، ولا يكتوون وعلى ربهم يتوكلون"

ኢብን ዓባስ ﷺ እና ሌሎችም ባስተላለፉት ሐዲስ የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

"ከአነርሱ ጋር ሰባ ሽ ሰዎች ያለምንም ሒሳብና ቅጣት ጀነት የሚገቡ ናቸው።" ከዚያም በሚከተለው ንግግራቸው አወሷቸው፡- "ከሰዎች ሩቅያን የማይፈልጉ ፣ በገድ የማያምኑ ፣ የማይተነሱ ፣ በጌታቸው የሚመኩ ናቸው።" *(ቡኻሪ፡ 5705, ሙስሊም፡ 218)*

ይህ በተውሒድ ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ ያለው ነው። እርሱም ተውሒድን ማረጋገጥና ማሟላት ነው።

ተውሒድን ማረጋገጥ ማለት ተውሒድን ማሟላት ፣ ማጠናቀቅ ፣ ከሽርክ ፣ ከቢድዓና ከተለያዩ ሐጢያቶች ማጽዳት እና ማጥራት ማለት ነው። ዑለሞች ወደአላህና ወደመጨረሻው አገር ለሚጓዝ ሰው ሶስት መሰናክሎች እንዳሉበት ይገልጻሉ። እነርሱም የማጋራት መሰናክል ፣ የቢድዓ መሰናክል እና የወንጀል መሰናክል ናቸው።

የሽርክ መሰናክል፡ ለአላህ አምልኮን ፍጹም በማጥራት ከማጋራት መሰናክል መጽዳት ይቻላል። ሱናን አጥብቆ በመያዝ ፣ ረሡልን ﷺ በመከተልና በእርሳቸው ጎዳና በመጓዝ ከቢድዓ መሰናክል መጽዳት ይቻላል። ከወንጀል ላይ መውደቅን በመጠንቀቅና ከወንጀል እና ከሐጢያት በወደቀ ጊዜ ፈጥኖ ወደአላህ ጸጸት በማድረግ ከወንጀል መሰናክል መጽዳት ይቻላል። አንድ ባሪያ ከዚህ ደረጃ ከደረሰ ተውሒድን በትክክል አረጋግጧል ማለት ይቻላል።

ተውሒድን ማረጋገጥ ሁለት ደረጃዎች አሉት። ዋጅብ (ግዴታ) እና ሙስተሀብ (ተወዳጅ ነገሮች) ናቸው። የሁለቱም ደረጃዎች ባለቤቶች ያለምንም ሒሳብና ቅጣት ጀነትን ይገባሉ።

ተውሒድን የማረጋገጥ የመጀመሪያው ደረጃ፡ የሙቅተሲዶች (የመካከለኞች) ደረጃ ነው።

ሙቅተሲድ፡ ማለት ዋጅብን (ግዴታዎችን) የፈጸመ ከሀራም የራቀ ማለት ነው። እንዲህ አይነት ባህሪ ያለው ሰው ተውሒድን በማረጋገጡ ከሙቅተሲዶች (ከመካከለኞች) ሆነ ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች ያለምንም ሂሳብና ቅጣት ጀነት ይገባሉ። ይህ አንደኛው ደረጃ ነው።

ሁለተኛው ደረጃ፡ ከመጀመሪያው ደረጃ ከፍ ይላል። ይህም ዋጅብ ከሆኑ ነገሮች ባሻገር ተወዳጅ ነገሮችን በመፈጸም ተውሒድን ማረጋገጥ ነው። ይህ ደረጃ የመልካም ቀዳሚዎች (ሳቢቆች) ደረጃ ነው። በዚህ ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች ዋጅብና ግዴታ ነገሮችን ተጠባብቀው ይሰራሉ ፣ ከባድ ወንጀሎችንና ሀራሞችን ይርቃሉ ፣ ይህ ብቻ አይደለም ተፈላጊ የሆኑ ሱናዎችን በመስራት ላይ ተሸቀዳዳሚ ናቸው።

እነዚህ በሁለቱም ክፍል ያሉ ተውሂድን አረጋጋጭ ሰዎች - ሙቅተሲድና በመልካም ተሸቀዳዳሚዎች - የትንሳኤ ቀን ያለምንም ሂሳብና ቅጣት ጀነትን ይገባሉ።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿ثُمَّ أَوْرَثْنَا الْكِتَابَ الَّذِينَ اصْطَفَيْنَا مِنْ عِبَادِنَا فَمِنْهُمْ ظَالِمٌ لِّنَفْسِهِ وَمِنْهُم مُّقْتَصِدٌ وَمِنْهُمْ سَابِقٌ بِالْخَيْرَاتِ بِإِذْنِ اللَّهِ ذَلِكَ هُوَ الْفَضْلُ الْكَبِيرُ﴾

"ከዚያም እነዚያን ከባሮቻችን የመረጥናቸውን መጽሐፉን አወረስናቸው። ከእነርሱም ነፍሱን በዳይ አልከ። ከእነርሱም መካከለኛ አልከ። ከእነሱም በአላህ ፈቃድ በበጎ ስራዎች ቀዳሚ አልከ። ያ (ማውረስ) ፤ እርሱ ታላቅ ችሮታ ነው።"

(ፋጢር፡ 32)

ሶስቱም ክፍሎች - ነፍሱን በዳይ ፣ ሙቅተሲድ (መካከለኛዎች) እና በመልካም ተሸቀዳዳሚዎች - ዘውታሪ የሆኑ ገነቶችን ይገባሉ።

ሙቅተሲድ እና በመልካም ተሸቀዳዳሚዎች፡ ያለምንም ሂሳብ ጀነት ይገባሉ።

ከሽርክ በታች በሆኑ ወንጀሎች ነፍሳቸውን በዳዮች ደግሞ ጀነትን ይገባሉ። ነገር ግን ነፍሳቸውን የበደሉት ልክ እንደ ሙቅተሲድና በመልካም ቀዳሚዎች ያለምንም ሂሳብና ቅጣት መጀመሪያ ጀነትን አይገቡም። ይልቁንም ለቅጣትና ለሂሳብ ይቀርባሉ። በአላህ መሸአ ውስጥ ናቸው። አላህ ከፈለገ ቀጥቶ ጀነት ያስገባቸዋል ወይም ምህረት ያደርግላቸዋል።

አራተኛው አንኳር ነጥብ

የተውሒድ አፍራሽና አጉዳዮች

ተውሒድ የራሱ የሆነ አፍራሽና አጉዳይ አለው። የተውሒድ አፍራሾች ስራን የሚያሰርዙ ሀይማኖቱን በአጠቃላይ የሚያበላሹ ናቸው። እነርሱም በአላህ መካድ፣ ማጋራትና ጥርት ያሉ ንፍቅናዎች ናቸው። የክህደት ፣ የማጋራት እና የትልቁ ንፍቅና አይነቶች ከመሰረቱ ተውሂድን ያፈርሱታል ፣ ይንዱታል።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጹ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿لَئِنْ أَشْرَكْتَ لَيَحْبَطَنَّ عَمَلُكَ وَلَتَكُونَنَّ مِنَ الْخَاسِرِينَ﴾

"ብታጋራ ስራህ በእርግጥ ይታበሳል። በእርግጥም ከከሃዲዎቹ ትሆናለህ ማለት ወደ አንተም ወደእነዚያም ካንተ በፊት ወደነበሩት በእርግጥ ተወርዷል።" (አዝ ዙመር ፡65)

የተውሒድ አጉዳዮች፡ ማለት ደግሞ ተውሒድን ሙሉ በሙሉ የማያበላሽ የማይንድ ነገር ግን የሚቀንስ ነው። ከነዚህ መካከል ትንሹ ክህደትና ተግባራዊ የሆነው ንፍቅና ናቸው ።

የአላህ መልእክተኛ ﷺ በሚከተለው ሐዲስ ተናግረዋል፡-

"آية المنافق ثلاث: إذا حدث كذب ، وإذا وعد أخلف ، وإذا اؤتمن خان"

"የመናፍቃን ምልክት ሶስት ናቸው፡ ሲያወራ ይዋሻል ፣ ቃል ሲገባ ያፈርሳል ፣ ሲያምኑት ይከዳል" (ቡኻሪ፡ 33, ሙስሊም፡ 59)

ይህ ተውሒድን የሚቀንስ ነው። እነዚህ ነገሮች ከባሪያው ላይ ከተገኙ ተውሒዱን እና ኢማኑን ያጎድሉታል። ትንሹ ማጋራት ፣ ማጋራትን ሳያስብ በአንደበቱ የማጋራት ቃላትን

መናገር ተውሂድን ይቀንሳል። ነገር ግን ማጋራትን አስቦ ከሆነ ተውሒዱን ሙሉ በሙሉ ከሚያፈርሱት ትልቁ ማጋራት ውስጥ የሚገባ ይሆናል።

በዚህ ምክንያት እያንዳንዱ አማኝ ሙሉ በሙሉ አፍራሽም ይሁን አጉዳይ ነገሮችን በመራቅ ተውሒዱን መጠበቅ ፣ መንከባከብ ይኖርበታል።

ሸይኽ ዓብዱረህማን ብን ሀሰን - ረሂመሁሏህ - የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

((የተውሒድ ተቃራኒ ሽርክ መሆኑን እወቅ። እነርሱም ሶስት አይነቶች ሲሆኑ ትልቁ ማጋራት ፣ ትንሹ ማጋራት እና ድብቁ ማጋራት ናቸው።

ለትልቁ ማጋራት መረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው፡-

﴿إِنَّ اللهَ لاَ يَغْفِرُ أَن يُشْرَكَ بِهِ وَيَغْفِرُ مَا دُونَ ذَلِكَ لِمَن يَشَاء وَمَن يُشْرِكْ بِاللهِ فَقَدْ ضَلَّ ضَلاَلاً بَعِيدًا﴾

"አላህ በርሱ የሚጋራትን (ወንጀል) አይምርም። ከዚህም ወዲያ ያለውን ለሚሻው ሰው ይምራል። በአላህም የሚያጋራ ሰው (ከእውነት) የራቀን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ።" (አን'ኒሳእ፡ 116)

﴿وَقَالَ الْمَسِيحُ يَا بَنِي إِسْرَائِيلَ اعْبُدُواْ اللهَ رَبِّي وَرَبَّكُمْ إِنَّهُ مَن يُشْرِكْ بِاللهِ فَقَدْ حَرَّمَ اللهُ عَلَيهِ الْجَنَّةَ وَمَأْوَاهُ النَّارُ وَمَا لِلظَّالِمِينَ مِنْ أَنصَارٍ﴾

"አልመሲህም አለ፡- "የእስራኤል ልጆች ሆይ! ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ።" እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ። መኖሪያውም እሳት ናት። ከበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም።" (አል'ማኢዳህ፡ 72)

ይህ አይነቱ ማጋራት አራት አይነት ክፍሎች አሉት፡-

አንደኛው አይነት፣ የተማጽኖ ወይም የጥሪ ማጋራት

ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው፣ -

﴿فَإِذَا رَكِبُوا فِي الْفُلْكِ دَعَوُا اللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ فَلَمَّا نَجَّاهُمْ إِلَى الْبَرِّ إِذَا هُمْ يُشْرِكُونَ۞لِيَكْفُرُوا بِمَا آتَيْنَاهُمْ وَلِيَتَمَتَّعُوا فَسَوْفَ يَعْلَمُونَ﴾

"በመርከቦች ውስጥ በተሳፈሩ ጊዜም አላህን መገዛትን ከእርሱ ብቻ ያጠሩ ሆነው ይጠሩታል። ወደየብስ (በማውጣት) ባዳናቸው ጊዜም ወዲያውኑ እነርሱ (ጣዖትን) ያጋራሉ። በሰጠናቸው ጸጋ ኪክዱና ኪጠቃቀሙ (ያጋራሉ)። ወደፊትም (የሚጠብቃቸውን) ያውቃሉ።" *(አል'ዓንከቡት፣ 65-66)*

ሁለተኛው አይነት፣ - በሀሳብ በፍላጎትና በአላማ ማጋራት

ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው።

﴿مَن كَانَ يُرِيدُ الْحَيَاةَ الدُّنْيَا وَزِينَتَهَا نُوَفِّ إِلَيْهِمْ أَعْمَالَهُمْ فِيهَا وَهُمْ فِيهَا لاَ يُبْخَسُونَ۞أُوْلَئِكَ الَّذِينَ لَيْسَ لَهُمْ فِي الآخِرَةِ إِلاَّ النَّارُ وَحَبِطَ مَا صَنَعُواْ فِيهَا وَبَاطِلٌ مَّا كَانُواْ يَعْمَلُونَ﴾

"ቅርቢቱን ሕይወትና ጌጧን የሚሹ የሆኑትን ሰዎች ስራዎቻቸውን (ምንዳዋን) በእርሷ ውስጥ ወደነሱ እንሞላላቸዋለን። እነሱም በርሷ ውስጥ ምንም አይጎድልባቸውም። እነዚያ እነርሱ በመጨረሻይቱ ዓለም ከእነርሱ ከእሳት በቀር የሌላቸው ናቸው። የሰሩትም ስራ በርሷ ውስጥ ተበላሸ። (በቅርቢቱ ዓለም) ይሰሩት የነበሩትም በጎ ስራ ብልሹ ነው።" *(ሁድ፣ 15-16)*

ሶስተኛው አይነት፣ የመታዘዝ ማጋራት

ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው ቁርኣናዊ አንቀጽ ነው፣ -

﴿اتَّخَذُواْ أَحْبَارَهُمْ وَرُهْبَانَهُمْ أَرْبَابًا مِّن دُونِ اللّهِ وَالْمَسِيحَ ابْنَ مَرْيَمَ وَمَا أُمِرُواْ إِلاَّ لِيَعْبُدُواْ إِلَـهًا وَاحِدًا لاَّ إِلَهَ إِلاَّ هُوَ سُبْحَانَهُ عَمَّا يُشْرِكُونَ﴾

"ከእርሱ በቀር ኬላ አምላክ የኬለውን አንድን አምላክ ኪገዙ እንጂ ያልታዘዙ ሲሆኑ ኪቃውንቶቻቸውንና መነኮሳታቸውን ፣ የመርየምን ልጅ አልመሲሀንም ከአላህ ኬላ አማልክት አድርገው ያዙ። ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው።" (አት'ተውባህ፡ 31)

ይህን ቁርአናዊ አንቀጽ አስመልክቶ ረሡል ﷺ ለዓድይ ብን ሀቲም ﷺ የሰጡት ትንታኔ ምንም አይነት ችግር የሌለበት ተስማሚ ትንታኔ ነው። የአላህ መልክተኛ ﷺ ለዓድይ ጥያቄ አቀረቡ "እኛ እኮ አንገዛቸውም" የሚል ምላሽ ሰጠ። ረሡልም እነሱን በመማጸን ብቻ ሳይሆን ክልክል በሆኑ ነገሮች እንኳ እውቀት ያላቸውንና ያለእውቀት አላህን እንገዛለን የሚሉ ባህታውያንን መታዘዝ አምልኮት እንደሆነ ለዓድይ ግልጽ አደረጉለት።

አራተኛው አይነት፡ በፍቅር ማጋራት

ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው ቁርአናዊ አንቀጽ ነው፡ -

﴿وَمِنَ النَّاسِ مَن يَتَّخِذُ مِن دُونِ اللّهِ أَندَاداً يُحِبُّونَهُمْ كَحُبِّ اللّهِ وَالَّذِينَ آمَنُواْ أَشَدُّ حُبًّا لِّلّهِ وَلَوْ يَرَى الَّذِينَ ظَلَمُواْ إِذْ يَرَوْنَ الْعَذَابَ أَنَّ الْقُوَّةَ لِلّهِ جَمِيعاً وَأَنَّ اللّهَ شَدِيدُ الْعَذَابِ﴾

"ከሰዎችም ከአላህ ኬላ ባካንጣዎችን (ጣዖታትን) አላህን እንደሚወዱ የሚወዷቸው ሆነው የሚይዙ አልኩ። እነዚያ ያመኑትም አላህን በመውደድ (ከእነርሱ) ይበልጥ የበረቱ ናቸው። እነዚያም የበደኩት ሰዎች ቅጣትን (በትንሳኤ ቀን) ባዩ ጊዜ ሃይል ሁሉ ከአላህ ብቻ መሆኑንና አላህም ቅጣቱ ብርቱ

መሆኑን (በዚህ አከም) ቢያውቁ ኖሮ (ባካንጣዎችን በመያዛቸው በተጸጸቱ ነበር)።" (አል'በቀራህ፡ 165)

ሁለተኛው የማጋራት አይነት ፡ ትንሹ ማጋራት

እርሱም ሪያእ (ይዩልኝ) ነው።

ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው ቁርኣናዊ አንቀጽ ነው፡-

﴿فَمَن كَانَ يَرْجُو لِقَاءَ رَبِّهِ فَلْيَعْمَلْ عَمَلًا صَالِحًا وَلَا يُشْرِكْ بِعِبَادَةِ رَبِّهِ أَحَدًا﴾

"የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው ፤ መልካም ስራን ይስራ። በጌታውም መገዛት አንድንም አያጋራ" በላቸው።" (አል'ከህፍ፡ 110)

ሶስተኛው የማጋራት አይነት ፡ ድብቅ ማጋራት

ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው የረሡል ﷺ ቃል ነው።

"الشرك في هذه الأمة أخفى من دبيب النمل على الصفاة السوداء في ظلمة الليل" ، وكفارته قوله ﷺ: "اللهم إني أعوذ بك أن أشرك بك شيئا وأنا أعلم ، وأستغفرك من الذنب الذي لا أعلم"

"በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ያለው ማጋራት በሌሊት ጨለማ ፣ በጥቁር ልሙጥ ዲንጋይ ላይ አንደምትንቀሳቀስ ጥቁር ጉንዳን ኮቴ የተደበቀ ነው።" ለዚህ ወንጀል መሰረዣው የሚከተለው ዱዓ ነው፡-

"አላህ ሆይ! አያወቅሁ በአንተ ከማጋራት አጠበቃለሁ ፤ ከማላቀውም ወንጀል ደግሞ ይቅርታን አጠይቅሃለሁ" (አቡ የዕላ፡ 60, ኢብኑ ሂባን ፊ"አል'መጅሩሂን"፡ 3/130, አልባኒ ሑዲሱን ሶሂህ ብለውታል "ሶሂህ አል'ጃሚዕ"፡ 3731)

ክህደት ሁለት አይነት ነው።

የመጀመሪያው ከኢስላም የሚያስወጣው ሲሆን ይህ ዓይነቱ ክህደት አምስት አይነት ክፍሎች አሉት።

አንደኛው፡ የማስተባበል ክህደት

ለዚህ ማስረጃ የሚሆነው የሚከተለው የአላህ ቃል ነው፡-

﴿وَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّنِ افْتَرَى عَلَى اللَّهِ كَذِبًا أَوْ كَذَّبَ بِالْحَقِّ لَمَّا جَاءَهُ أَلَيْسَ فِي جَهَنَّمَ مَثْوًى لِّلْكَافِرِينَ﴾

"በአላህም ላይም ውሸትን ከቀጣጠፈ ሰው ወይም እውነቱ በመጣለት ጊዜ ከአስዋሽ ይበልጥ በዳይ ማነው በገሀነም ውስጥ ለከሃዲዎች መኖሪያ የለምን?"

(አል'አንከቡት፡ 68)

ሁለተኛው፡ የኩራት ወይም የእምቢተኝነት ክህደት

ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው ቁኣናዊ አንቀጽ ነው፡-

﴿وَإِذْ قُلْنَا لِلْمَلاَئِكَةِ اسْجُدُواْ لآدَمَ فَسَجَدُواْ إِلاَّ إِبْلِيسَ أَبَى وَاسْتَكْبَرَ وَكَانَ مِنَ الْكَافِرِينَ﴾

"ከመላእክትም "ለአደም ስገዱ" ባልን ጊዜ (አስታውስ)። ሁሉም ወዲያውኑ ሰገዱ ፤ ኢብሊስ ብቻ ሲቀር እምቢ አለ ፤ ኩራም ከከሃዲዎቹም ሆነ።" *(አል'በቀራህ፡ 34)*

ሶስተኛው፡ - የመጠራጠር ክህደት

ማስረጃው የሚከተለው ቁርኣናዊ አንቀጽ ነው፡-

﴿وَدَخَلَ جَنَّتَهُ وَهُوَ ظَالِمٌ لِّنَفْسِهِ قَالَ مَا أَظُنُّ أَن تَبِيدَ هَذِهِ أَبَدًا﴿وَمَا أَظُنُّ السَّاعَةَ قَائِمَةً وَلَئِن رُّدِدتُّ إِلَى رَبِّي لَأَجِدَنَّ خَيْرًا مِّنْهَا مُنقَلَبًا﴿قَالَ لَهُ صَاحِبُهُ وَهُوَ يُحَاوِرُهُ أَكَفَرْتَ بِالَّذِي خَلَقَكَ مِن تُرَابٍ ثُمَّ مِن نُّطْفَةٍ ثُمَّ سَوَّاكَ رَجُلًا﴾

“እርሱም ነፍሱን በዳይ ሆኖ ወደ አትክልቱ ገባ። “ይህች ዘላለም ትጠፋለች ብዬ አልጠረጥርም” አለ። “ሰዓቲቱንም ቋሚ (ኋኝ) ናት ብዬ አልጠረጥርም። (እንደምትለው) ወደ ጌታየም ብመለስ ከእርሷ የበለጠን መመለሻ በእርግጥ አገኛለሁ” (አለው)። ጓደኛው (አማኙ) እርሱ ከእርሱ የሚመካለው ሲሆን “በዚህ ከዐፈር ፣ ከዚያም ከፍትወት ጠብታ ከፈጠረህ፣ ከዚያም ሰው ባደረገህ (አምላክ) ካድከን?” አለው።” *(አል’ከህፍ፡ 35-37)*

አራተኛው፡- የመዘር ወይም የመቱው ክህደት

ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው ቁርኣናዊ አንቀጽ ነው፡-

﴿وَالَّذِينَ كَفَرُوا عَمَّا أُنذِرُوا مُعْرِضُونَ﴾

“እነዚያም የካዱትም ከተሰፈራሩት ነገር (ትተው) ዟሪዎች ናቸው።” *(አል'አህቃፍ፡ 3)*

አምስተኛው፡ የንፍቅና ክህደት

ለዚህ ማስረጃ የሚከተለው ቁርኣናዊ አንቀጽ ነው፡-

﴿ذَلِكَ بِأَنَّهُمْ آمَنُوا ثُمَّ كَفَرُوا فَطُبِعَ عَلَى قُلُوبِهِمْ فَهُمْ لَا يَفْقَهُونَ﴾

“ይህ እነርሱ (በምላስ) ያመኑ ከዚያም (በልብ) የካዱ በመሆናቸው ነው። በልቦቻቸውም ላይ ታተመባቸው ፤ ስለዚህ እነርሱ አያውቁም ” *(አል'ሙናፊቁን፡ 3)*

ከኢስላም የሚያስወጣ ትንሹ ክህደት፡ በጸጋ መካድ

ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው ቁርኣናዊ አንቀጽ ነው፡-

﴿وَضَرَبَ اللَّهُ مَثَلاً قَرْيَةً كَانَتْ آمِنَةً مُّطْمَئِنَّةً يَأْتِيهَا رِزْقُهَا رَغَدًا مِّن كُلِّ مَكَانٍ فَكَفَرَتْ بِأَنْعُمِ اللَّهِ فَأَذَاقَهَا اللَّهُ لِبَاسَ الْجُوعِ وَالْخَوْفِ بِمَا كَانُواْ يَصْنَعُونَ﴾

"አላህ ጸጥተኛ ፣ የረካች ፣ ሲሳይዋ ሰፊ ሆኖ ከየስፍራው ይመጣላት የነበረችውንና በአላህ ጸጋዎች የካደችውን አላህም ይሰሩት በነበሩት ሃጢኣት የረሃብንና የፍርሃትን ቅጣቶች ያቀመሳትን ከተማ (መካን) ምሳሌ አደረገ።"

(አን'ነሕል፡ 112)

﴿إِنَّ الإِنسَانَ لَظَلُومٌ كَفَّارٌ﴾

"ሰው በጣም በደከኛ ከሃዲ ነው።" *(ኢብራሂም፡ 34)*

ንፍቅና በሁለት የሚከፈል ሲሆን እርሱም ኒፋቁን ኢዕቲቃድይ (እምነታዊ ንፍቅና) እና ኒፋቁል ዓመልይ (ተግባራዊ ንፍቅና) ናቸው።

ኢዕቲቃድይ (እምነታዊ)፡ የሚባለው ስድስት ክፍሎች አሉት።

ረሡልን ﷺ ማስተባበል ወይም ረሡል ﷺ ከመጡበት በከፊሉ ማስተባበል ወይም ረሱልን መጥላት ወይም ረሱል ከመጡበት ነገር በአንዱ መጥላት ወይም የረሡል ﷺ ዲን ዝቅ ሲል ወይም ውርደት ሲገጥመው መደሰት ወይም የረሡል ﷺ ዲን ድል ሲጎናጸፍ መጥላት ናቸው።

ከእነዚህ ስድስት አይነቶች አንዱን የፈጸመ በጣም አዘቅጥ በሆነ እሳት ውስጥ ይገባል።

ከንፍቅና ፣ ከጭቅጭቅና ከኩራት በአላህ እንጠበቃለን!

ኒፋቅ አል'ዓመልይ (ተግባራዊ የሆነው ንፍቅና) የሚባለው አምስት ክፍሎች አሉት።

በውሸት መናገር ፣ በሐሰት መከራከር ፣ ቃል ገብቶ ማፍረስ ፣ ሰዎች ሲያምኑት መሸወድ ፣ ቀጠሮን ማፍረስ ናቸው።)) *"ዱረሩ አሰሰንያ" 3/66*

አምስተኛው አንኳር ነጥብ

የተውሒድ መሰረቱና ምንጩ

ተውሒድ ከሰማይ የወረደ ፣ ከቁርኣን እና ከሐዲስ የመነጨ ትክክለኛ ፣ ቀጥ ያለው ብቸኛ እምነት ነው። ከሰዎች ጋር ያለው እምነት ከምድር የተፈበረከ በመሆኑ የተውሒድ ተጻራሪ ወይም ተቃራኒ ነው። የተውሒድ እምነት አላህ ለባሮቹ የሚወደው እምነት ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَرَضِيتُ لَكُمُ الإِسْلاَمَ دِينًا﴾

"ከእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ" (አል'ማኢዳህ፡ 3)

﴿وَمَن يَبْتَغِ غَيْرَ الإِسْلاَمِ دِينًا فَلَن يُقْبَلَ مِنْهُ﴾

"ከኢስላም ኬላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም።"
(አል'ዒምራን፡ 85)

﴿وَمَن يَرْغَبُ عَن مِّلَّةِ إِبْرَاهِيمَ إِلاَّ مَن سَفِهَ نَفْسَهُ﴾

"ከኢብራሒምም ሀግጋት ነፍሱን ያቄለ ሰው ካልሆነ በስተቀር የሚያፈገፍግ ማነው?" (አል'በቀራህ 130)

﴿إِنَّ الدِّينَ عِندَ اللهِ الإِسْلاَمُ﴾

"ከአላህ ዘንድ (የተወደደ) ሃይማኖት ኢስላም ብቻ ነው" (አል'ዒምራን፡ 19)

ተውሒድ በባሮች ላይ ያወረደው የሆነ የአላህ ትዕዛዝ ነው። ተውሒድ ለእርሱ ሲባልና እርሱን ለማረጋገጥ ፍጥረታቶችን የፈጠረበት እና ያስገኘበት የአላህ ዲን ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَلَقَدْ بَعَثْنَا فِي كُلِّ أُمَّةٍ رَّسُولاً أَنِ اعْبُدُواْ اللّهَ وَاجْتَنِبُواْ الطَّاغُوتَ﴾

"በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ "አላህን ተገዙ ፤ ጣዖትንም ራቁ" በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል።" *(አን'ነሕል፡36)*

﴿أَتَى أَمْرُ اللّهِ فَلاَ تَسْتَعْجِلُوهُ سُبْحَانَهُ وَتَعَالَى عَمَّا يُشْرِكُونَ۞يُنَزِّلُ الْمَلآئِكَةَ بِالْرُّوحِ مِنْ أَمْرِهِ عَلَى مَن يَشَاء مِنْ عِبَادِهِ أَنْ أَنذِرُواْ أَنَّهُ لاَ إِلَهَ إِلاَّ أَنَاْ فَاتَّقُونِ﴾

"የአላህ ትዕዛዝ መጣ ፤ ስለዚህ አታስቸኩሉት ፤ ከሚይገባው ሁሉ ጠራ ከሚያጋሩትም ሁሉ ላቀ፤ ከባሮቹ በሚሻው ሰው ላይ መላእክትን ከራእይ ጋር በፈቃዱ ያወርዳል (ከሐዲዎችን በቅጣት) አስጠንቅቁ ፤ እነሆ ከኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም ፤ ፍሩኝም ማለትን (አስታውቁ በማለት ያወርዳል) ።" *(አን'ነሕል፡1-2)*

ከተውሒድ ውጭ የሚገኙ እምነቶች ሁሉ ሰው ሰራሽ ፣ ሰዎች ያስገኙዋቸው ምድር በቀል እምነቶች ናቸው። በዚህ ምክንያት በሰዎች መካከል ያሉትን ሸርክ ፣ ክህደት ፣ ኒፋቅ እና ሌላም የጥመት አይነቶችን ወህይ (ራዕይ) ያልወረደባቸውን እምነቶች ከንቱ ማድረግ ከነብያቶች መንገድና አላማ አንዱ ነው።

ዩሱፍ ለእስር ቤት ጓደኞቹ ምን እንደተናገረ አላህ እንደሚከተለው ገልጾልናል፡-

﴿يَا صَاحِبَيِ السِّجْنِ أَأَرْبَابٌ مُّتَفَرِّقُونَ خَيْرٌ أَمِ اللّهُ الْوَاحِدُ الْقَهَّارُ۞مَا تَعْبُدُونَ مِن دُونِهِ إِلاَّ أَسْمَاء سَمَّيْتُمُوهَا أَنتُمْ وَآبَآؤُكُم مَّا أَنزَلَ اللّهُ بِهَا مِن سُلْطَانٍ إِنِ الْحُكْمُ إِلاَّ لِلّهِ أَمَرَ أَلاَّ تَعْبُدُواْ إِلاَّ إِيَّاهُ ذَلِكَ الدِّينُ الْقَيِّمُ وَلَكِنَّ أَكْثَرَ النَّاسِ لاَ يَعْلَمُونَ﴾

"የእስር ቤት ጓደኞቼ ሆይ! የተለያዩ አምላኮች ይሻላሉን? ወይስ አሸናፊው አንዱ

አላህ "ከእርሱ ኬላ እናንተና አባቶቻችሁ (አሚልክት ብላችሁ) የጠራችኋቸውን ስሞች እንጅ አትገዙም። አላህ በእርሷ ምንም አስረጅ አላወረደም። ፍርዱ የአላህ እንጅ የኬላ አይደለም። እርሱን እንጅ ኬላን እንዳትገዙ አዟል። ይህ ትክክለኛው ሃይማኖት ነው። ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም።" (ዩሱፍ: 39-40)

﴿أَفَرَأَيْتُمُ اللَّاتَ وَالْعُزَّى۞وَمَنَاةَ الثَّالِثَةَ الْأُخْرَى۞أَلَكُمُ الذَّكَرُ وَلَهُ الْأُنثَى۞تِلْكَ إِذًا قِسْمَةٌ ضِيزَى۞إِنْ هِيَ إِلَّا أَسْمَاء سَمَّيْتُمُوهَا أَنتُمْ وَآبَاؤُكُم مَّا أَنزَلَ اللَّهُ بِهَا مِن سُلْطَانٍ إِن يَتَّبِعُونَ إِلَّا الظَّنَّ وَمَا تَهْوَى الْأَنفُسُ وَلَقَدْ جَاءهُم مِّن رَّبِّهِمُ الْهُدَى﴾

"አልካትንና አልዑዛን አያችሁን? ሶስተኛይቱንም አነስተኛዋን መናትን (አያችሁን? የምትገዟቸው ሃይል አላቸውን?) ከእናንተ ወንድ ከእርሱም ሴት (ልጅ) ይኖራልን? ይህቺ ያን ጊዜ አድሏዊ ክፍያ ናት። እነርሱ እናንተና አባቶቻችሁ (አሚልክት ብላችሁ) የጠራችኋቸው ስሞች ብቻ እንጅ ምንም አይደሉም።" (አን'ኒጅም: 19-23)

ሁድ ለህዝቦቹ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿أَتُجَادِلُونَنِي فِي أَسْمَاء سَمَّيْتُمُوهَا أَنتُمْ وَآبَآؤُكُم مَّا نَزَّلَ اللّهُ بِهَا مِن سُلْطَانٍ فَانتَظِرُواْ إِنِّي مَعَكُم مِّنَ الْمُنتَظِرِينَ﴾

"እናንተና አባቶቻችሁም (አሚልክት ብላችሁ) በጠራችኋቸው ስሞች አላህ በእርሷ ምንም ማስረጃ ያላወረደባት ስትሆን ትከራከሩኛላችሁን? ተጠባበቁም እኔ ከእናንተ ጋር ከተጠባባቂዎቹ ነኝና" አለ።" (አል'አዕራፍ: 71)

የተውሒድ ምንጭ የአላህ ኪታብ እና የነብዩ ﷺ ሱና ናቸው።

ተውሒድ የተያዘው ከንጹህና ጥርት ካለው ምንጭ ነው። ከሰዎች ዘንድ ያለው ዓቂዳ ወይም እምነት ምንጩ አንድም የተበላሸ እና የከሰረ ከሆነ የአዕምሮ አመለካከት ሲሆን ወይም አመጸኛ ከሆነው የሰይጣን ወህይ (ራዕይ) ነው። ወህይ ሲባል ሁለት አይነት ነው። አንደኛው ከአላህ የሆነ ወህይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከሰይጣን የሆነ ወህይ ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَإِنَّ الشَّيَاطِينَ لَيُوحُونَ إِلَى أَوْلِيَآئِهِمْ لِيُجَادِلُوكُمْ وَإِنْ أَطَعْتُمُوهُمْ إِنَّكُمْ لَمُشْرِكُونَ﴾

"ሰይጣናትም ወደ ወዳጆቻቸው (በክትን በመብላት) ይከራከሯችሁ ዘንድ ይሾካሾካሉ። ብትታዘዙዋቸውም እናንተ በእርግጥ አጋሪዎች ናችሁ።" (አል'አንዓም፡ 121)

﴿وَلِتَصْغَى إِلَيْهِ أَفْئِدَةُ الَّذِينَ لاَ يُؤْمِنُونَ بِالآخِرَةِ وَلِيَرْضَوْهُ وَلِيَقْتَرِفُواْ مَا هُم مُّقْتَرِفُونَ﴾

"እንደዚሁም ከነቢያት ሁሉ ከሰውና ከጅን የሆኑን ሰየጣናት ጠላት አደረግን። ከፊላቸው ወደ ከፊሉ ከሚታከል ክብለብለን ቃል ይጥላሉ።" (አል'አንዓም፡ 112)

﴿تَنَزَّلُ عَلَى كُلِّ أَفَّاكٍ أَثِيمٍ﴾

"በውሸታም ሃጢአተኛ ሁሉ ላይ ይወርዳሉ።" (አሽ'ሹዓራእ፡ 222)

(ነብይ ነኝ ብሎ የሞገተው) ሙኽታር ብን አቢ ዑበይድ በዚህ ክፍል ውስጥ ይመደባል።

"ሙኽታር ወህይ ይወረድልኛል በማለት ይሞግታል ይህ ጉዳይ እንዴት ይታያል?" የሚል ጥያቄ ለኢብን ዑመርና ለኢብን ዓባስ (ረዲየሏሁ ዓንሁማ) ቀረበላቸው።

እንደኛው ሶሃባ የሚከተለውን የአላህ ቃል አነበበ፡-

﴿وَلِتَصْغَى إِلَيْهِ أَفْئِدَةُ الَّذِينَ لاَ يُؤْمِنُونَ بِالآخِرَةِ وَلِيَرْضَوْهُ وَلِيَقْتَرِفُواْ مَا هُم مُّقْتَرِفُونَ﴾

"ሰይጣናትም ወደ ወዳጆቻቸው (በክትን በመብላት) ይከራከሯችሁ ዘንድ ይሾካሾካሉ። ብትታዘዙዋቸውም እናንተ በእርግጥ አጋሪዎች ናችሁ።" (አል'አንዓም፡ 121)

ሌላኛው ሶሃባ ደግሞ የሚከተለውን ቁርኣናዊ አንቀጽ አነበበ፡-

﴿تَنَزَّلُ عَلَى كُلِّ أَفَّاكٍ أَثِيمٍ﴾

"ሰይጣናት በማን ላይ እንደሚወርዱ ልንገራችሁን?" (ሹዓራዕ፡221) *(መጅሙኣ ፈታዋ ሊብን ተይሚያ ፡ 13/75)*

ሰይጣን ወደጥመት ባለቤቶች የእምነት ፣ የአመለካከት ፣ የመጥፎ እሳቤን ፣ የጉትጎታ እና የቸኮታን ወህይ ያወርዳል። ሰዎች ከዚህ ሰይጣን ካወረደላቸው ወህይ ተነስተው በተለያዩ የጥመት አመለካከቶች ጥሪ ያደርጋሉ ፤ ወደርሷ ሰዎች የሚደርሱባት የሆኑ የተበላሹ ሰይጣናዊ መንፈሶችን ያሰራጫሉ ፤ ከዚያም ከዚህ ተነስተው "በልምድ አይተነዋል ወይም ሸይኾቻችን በልምድ ሞክረውታል" የሚል ማስረጃ በመያዝ አዳዲስ ዒባዳዎችን ስርዓቶችንና መንገዶችን ይፈበርካሉ።

ዲን ደግሞ በልምድ ወይም በህልም የሚያዝ ነገር አይደለም። "በህልሜ እንዲህ እንዲህ አይነት ነገር ተመለከትኩ" ይላል። ከዚያም በእርሱ ላይ ተንተርሶ ዲን ወይም ዓቂዳ ይመሰርታል። አብዛኛው ሰው አላህ ማስረጃ ባላወረደበት ነገር ላይ ተንተርሶ ነው ዓቂዳውን የሚመሰርተው።

ከእርሱ ውጭ ከእምነት የማይቀበለው የሆነው የተባረከው የአላህ ዲን የተውሂድ ዓቂዳ ነው። ይህ ተውሂድ ምንጩ የጠራ ነው። ከመጀመሪያው ንጹህ ምንጭ የቀዳ ሌሎችን ምንጮች የደፈረሱ ሆኖ ያገኛቸዋል።

ነገር ግን ትክክለኛና ጥርት ያለውን የአላህን የወህይ ምንጭ ያወቀ ካልሆነ በቀር የደፈረሰውን ምንጭ የሚያውቅ የለም። ለዚህ ነው በጥመት ፣ በሽርክ ላይ በነበሩበት ወቅት ትክክለኛ አዕምሮ ፣ ቀጥ ያለ ዲን ላይ እንደሆኑ የሚያስቡ ሰዎች አላህ ወደትክክለኛው የተውሂድ ጎዳና ከመራቸው በኋላ የነበሩበት ሽርክ ድፍርስ መሆኑን ፤ እነርሱም ከዚህ ቀደም የማይገነዘቡ ህዝቦች እንደነበሩ የሚገነዘቡት።

ሶሃቦች አንዳንዴ ተሰባስበው ወደኢስላም የመራቸውን ጌታ አላህን ለማመስገን ከዚህ በፊት የነበሩበትን የጃሂልያ ወይም የሽርክ ህይዎት ያስታውሳሉ።

አቢ ውስማን አንነህድይ የጃሂልያን ስርዓት ያገኘ ሰው ነበር። ረሡልን ﷺ ሳይመለከት በረሡል ዘመን እስልምናን ተቀብሎ ከዚህ በፊት የነበረውን ህይዎቱን እንደሚከተለው ያወሳ ነበር፦

“በጃሂልያ ጊዜ ዲንጋይን እናመልክ ነበር። “እናንተ ተንቫዎች ሆይ! ጌታችሁ ጠፋ! ጌታችሁን ፈልጉ” እያለ የሚጣራ ተጣሪ ሰማን። ዲንጋይ የሚያመልኩ ሰዎች ጠፉ ከሰሩ ለማለት ፈልጎ ነው። ይህ ጥሪ ባለበት ሁኔታ ሌላ የምናመልከው ዲንጋይ ይፈለጋል። ይሄው ጌታችሁን ወይም ተመሳሳዩን አገኘን በማለት ተጣሪው ይጣራል። ቀርበን ስንመለከት ዲንጋይ ነው። ከእርሱ (አምላክ ብለን ካዘጋጀነው) ዲንጋይ ላይ ግመል እናርድበታለን። ከጊዜ በኋላ ከማንኛውም ችግር እና ውርደት ተላቀቅን።”

ከዚህ ቀደም የነበረውን አይነት ወይም ተቀራራቢ ሌላ ዲንጋይ አገኙ። ይዘውት መጡ። ሊገዙት ፣ ተስፉ ሊያደርጉበት ፤ ሊማጸኑት ፣ እርድ ሊያርዱለት ወደርሱ ተቅጣጩ። የት ነው ያለው የእነዚህ ሰዎች አዕምሮ?

ይህን ተግባር እየፈጸሙ የአላህን ምርጥ ነብያቶችንና መልእክተኞችን እብድ በማለት ይሳደባሉ። የራሳቸውን ነፍስ ግን እንደ አስተዋይ ይቆጥራሉ። አንድ ሰው የተውሂድን ፣ የኢማንን እና የቅን ጎዳናን ችቦ አላህ በልቦናው ላይ ከለኮሰለት እስልምና ተውሒድ ምን እንደሆነ ግልጽ ይሆንለታል። ሙሽሪኮች ያሉበት መንገድ ፣ የሚደገፉበት ምንጭ የተበላሸ ፣ በጥመትና በውሸት የተሞላ ፣ የሙሽሪኮች አዕምሮ የተዛባ መሆኑ ግልጽ ይሆንለታል።

ስድስተኛው አንኳር ነጥብ

የተውሒድ ፍሬዎችና ጥቅሞች

ለተውሒድ ተቆጥረው የማይዘለቁ ጫፉን የማንደርስበት ፍሬዎችና ጥቅሞች አሉት። ይህን የሚጠቁመው የሚከተለው የአላህ ቁርኣናዊ አንቀጽ ነው፡-

﴿أَلَمْ تَرَ كَيْفَ ضَرَبَ اللهُ مَثَلاً كَلِمَةً طَيِّبَةً كَشَجَرَةٍ طَيِّبَةٍ أَصْلُهَا ثَابِتٌ وَفَرْعُهَا فِي السَّمَاءِ۞تُؤْتِي أُكُلَهَا كُلَّ حِينٍ بِإِذْنِ رَبِّهَا وَيَضْرِبُ اللهُ الأَمْثَالَ لِلنَّاسِ لَعَلَّهُمْ يَتَذَكَّرُونَ﴾

"አላህ መልካምን ቃል ሰሯ (በምድር ውስጥ) የተደላደለች ቅርንጫፏም ወደ ሰማይ (የረዘመች) እንደሆነች መልካም ዛፍ አድርጎ ምሳሌን እንዴት እንደገለጸ አላየኽምን?" ምግቧን (ፍሬዋን) በጌታዋ ፈቃድ በየጊዜው ትሰጣለች" *(ኢብራሂም፡ 24-25)*

ባሮች በዚህ ዓለምና በወዲያኛው ዓለም የሚያገኙዋቸው የተውሒድ ፍሬዎችና ጥቅሞች ገደብ የላቸውም። ይሁን እንጅ ከጥቅሞቹ መካከል ጥቅል የሆኑትን የተወሰኑትን እንደሚከተለው እናቀርባለን፡-

- **የሰው ልጅ በዚህ ዓለምም ይሁን በወዲያኛው ዓለም የሚያገኛቸው መልካም ነገሮች ከእርሱ ላይ የሚወገዱለት መጥፎ ክስተቶች በተውሒድ ፍሬና በእርሱው አሻራ ነው።** ዝርዝር ጥቅሞችን ከተመለከትን ትልቁ የተውሒድ ፍሬና ውጤት ስራን ማጥራቱና ንጹህ ማድረጉ ነው። በተውሒድ ካልሆነ በቀር የማንኛውም ሰው ስራ ከሰሪው ዘንድ ተቀባይነትን አያገኝም። ተውሒድ ለምንሰራቸው ስራዎች ልክ እንደህንጻ መሰረት ፤ ለዛፍ ደግሞ ልክ እንደ ስር መሰረቱ ነው።

ለዚህም አላህ የሚከተለውን ቁርኣናዊ አንቀጽ ተናግሯል፡-

﴿وَمَنْ أَرَادَ الآخِرَةَ وَسَعَى لَهَا سَعْيَهَا وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَأُولَئِكَ كَانَ سَعْيُهُم مَّشْكُورًا﴾

"መጨረሻይቱንም ዓለም የፈለገ ሰው እርሱ አማኝ ሆኖ ከርሷ (ተገቢ) ስራዋን የሰራም ሰው እነዚህ ስራቸው የተመሰገነ ይሆናል።" *(አል'ኢስራእ:19)*

﴿مَنْ عَمِلَ صَالِحًا مِّن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَى وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَلَنُحْيِيَنَّهُ حَيَاةً طَيِّبَةً وَلَنَجْزِيَنَّهُمْ أَجْرَهُم بِأَحْسَنِ مَا كَانُواْ يَعْمَلُونَ﴾

"ከወንድም ወይም ከሴት እርሱ አማኝ ሆኖ በጎን የሰራ መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን። ይሰሩትም ከነበሩት ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን።" *(አን'ነሕል:97)*

ተውሒድ የምንሰራቸውን ስራዎች ያጠራል ፣ ንጹህ ያደርጋል። ተውሒድ ከሌለ ከፍተኛና በርካታ ስራዎች ቢሰሩም ከአላህ ዘንድ ተቀባይነትን አያገኝም።

አላህ በተከበረው ቁርዓናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَمَا مَنَعَهُمْ أَن تُقْبَلَ مِنْهُمْ نَفَقَاتُهُمْ إِلاَّ أَنَّهُمْ كَفَرُواْ بِاللّهِ وَبِرَسُولِهِ وَلاَ يَأْتُونَ الصَّلاَةَ إِلاَّ وَهُمْ كُسَالَى وَلاَ يُنفِقُونَ إِلاَّ وَهُمْ كَارِهُونَ﴾

"ልግስናዎቻቸውን ከነሱ ተቀባይ የሚያገኙ ከመሆን እነሱ በአላህና በመልክተኛው የካዱ ፤ ሶላትንም እነሱ ታካቾች ሆነው በስተቀር የማይሰግዱ ፤ እነሱም ጠይዎች ሆነው በስተቀር የማይሰጡ መሆናቸው እንጂ ሌላ አልከለከላቸውም።" *(አት'ተውባህ: 54)*

﴿وَمَن يَكْفُرْ بِالإِيمَانِ فَقَدْ حَبِطَ عَمَلُهُ﴾

"ከእምነትም የሚመለስ (የሚክድ) ሰው በእርግጥ ስራው ተበላሸ"

(አል' ማኢዳህ: 5)

﴿وَلَقَدْ أُوحِيَ إِلَيْكَ وَإِلَى الَّذِينَ مِنْ قَبْلِكَ لَئِنْ أَشْرَكْتَ لَيَحْبَطَنَّ عَمَلُكَ وَلَتَكُونَنَّ مِنَ الْخَاسِرِينَ﴾

"ብታጋራ ስራህ በእርግጥ ይታበሳል። በእርግጥም ከከሃዲዎች ትሆናለህ ሚለት ወደ አንተም ወደእነዚያም ካንተ በፊት ወደነበሩት በእርግጥ ተወርዷል።" (አዝ ዙመር፡ 65)

- **ተውሒድ በዚህ ዓለምም ይሁን በወዲያኛው ዓለም ከቅጣት ነጻ የምንሆንበት ደረጃችን ከፍ የሚልበት ነው።**

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿أُوْلَئِكَ عَلَى هُدًى مِّن رَّبِّهِمْ وَأُوْلَئِكَ هُمُ الْمُفْلِحُونَ﴾

"እነዚያ ከጌታቸው በመመራት ላይ ናቸው፤ እነዚያም እነሱ ፍላጎታቸውን ያገኙ ናቸው።" (አል'በቀራህ፡ 5)

የተውሒድ ባለቤቶች ለቅኑ ጎዳና የተመሩ ፣ ከሚፈሩት ነገር ድነው የሚፈልጉትን ነገር የማግኘት ባለቤቶች ናቸው። **"ፈላህ"** የሚለው ቃል በመልካም ነገሮች ዙሪያ ታላቁ ንግግር ነው። **"ሙፍሊህ"** ማለት በዚህ ዓለምም ይሁን በወዲያኛው መልካም ነገሮችን የተጎናጸፈ ማለት ነው። በአላህ ተውሂድ አምልኮትን ወይም ዲንን ፍጹም ለአላህ በማጥራት ካልሆነ በቀር በዚህ ዓለምም ይሁን በወዲያኛው ዓለም መልካምን አያገኝም።

- ተውሒድ ከአላህ ዘንድ ክብርና ጀነትን ለማግኘት ከቅጣትና ከቁጣው ለመዳን ምክንያት ነው። የተውሒድ ሰው ሆኖ አላህን የተገናኘ ጀነትን ይገባል። በአላህ አጋሪ ሆኖ አላህን የተገናኘ ሰው ደግሞ እሳትን ይገባል ፤ ዘላለም በእርሷ ውስጥ ይዘወትራል። አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿إِنَّ اللّهَ لاَ يَغْفِرُ أَن يُشْرَكَ بِهِ وَيَغْفِرُ مَا دُونَ ذَلِكَ لِمَن يَشَاء وَمَن يُشْرِكْ بِاللّهِ فَقَدِ افْتَرَى إِثْمًا عَظِيمًا﴾

"አላህ በእርሱ ሚጋራትን በፍጹም አይምርም። ከዚህ ኬላ ያለውንም (ሐጢያት) ከሚሻው ሰው ይምራል። በአላህም የሚያጋራ ሰው ታላቅን ሃጢአት በእርግጥ ቀጠፈ።" (አን'ኒሳእ፡48)

ከተውሒድ ፋናዎቹ ጀነት ለመግባት ከእሳት ለመዳን ምክንያት መሆኑ ነው።

ግዴታ ከሆነውም ይሁን ተወዳጅ ከሆኑት የተውሒድ ክፍሎች ያረጋገጠ ዋስትናው እሳት ከመግባት ፍጹም መዳኑ ነው። ነገር ግን ከትልቁ ሽርክ ውጭ ወንጀሎችን የሚፈጽም የተውሂድ ሰው ከሆነ እሳት ከመዘውተር ነጻ ይሆናል ማለት ነው። አንድ ሰው ሙሽሪክ ካልሆነ እሳት ውስጥ አይዘወትርም።

ለዚህ ማስረጃው የሚከተለው ሐዲስ ነው፡-

"أمر الملائكة أن يخرجوا من النار من كان لا يشرك بالله شيئا ممن أراد الله تعالى أن يرحمه ممن يقول : لا إله إلا الله"

"አላህ ፣ በአርሱ ምንም ያላጋሩ "ላኢላሃ ኢልለላህ" (የሚለውን ቃል) የተናገሩ ሰዎችን ከእሳት አንዲያወጡ መላኢካዎችን ያዛል" (ቡኻሪ፡7437, ሙስሊም፡182)

- ተውሒድ ደረት እንዲሰፋ ያደርጋል። የደረቱ ስፋት እንደኢማኑ ሙሉነት ፣ ጥንካሬ እና ቁመራ ይወሰናል።

አላህ በተከበረው ቁርኣኑ የሚከተለውን ተናግሯል

﴿أَفَمَن شَرَحَ اللَّهُ صَدْرَهُ لِلْإِسْلَامِ فَهُوَ عَلَى نُورٍ مِّن رَّبِّهِ﴾

"አላህ ደረቱን ከእስልምና ያሰፋለትና እርሱም ከጌታው ዘንድ በብርሃን ላይ የሆነ ሰው (ልቡ እንደ ደረቀ ሰው ነውን)" (አዝ'ዙመር፡22)

﴿فَمَن يُرِدِ اللَّهُ أَن يَهْدِيَهُ يَشْرَحْ صَدْرَهُ لِلْإِسْلَامِ وَمَن يُرِدْ أَن يُضِلَّهُ يَجْعَلْ صَدْرَهُ ضَيِّقًا حَرَجًا كَأَنَّمَا يَصَّعَّدُ فِي السَّمَاءِ﴾

"አላህም ኪመራው የሚሻውን ሰው ደረቱን (ልቡን) ለኢስላም ይከፍትለታል። ኪያጠመውም የሚሻውን ሰው ደረቱን ጠባብ ችጋራ ወደ ሰማይ ከመውጣት እንደሚታገል ያደርገዋል።" (አል'አንዓም: 125)

ተውሒድ ወይም ወደቅኑ ጎዳና መመራት ደረትን ለመስፋት ፤ ማጋራትና ጥመት ደረትን ለማጣበብ ትልቁ ምክንያት ናቸው።

- **የተውሒድ ባለቤቶችን በልቅና በድል በዚህ ዓለም በምጀት ፣ ሁኔታዎችን በማስተካከልና ልቅና በመስጠት ዋስትና ወስዶላቸዋል።**

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَعَدَ اللَّهُ الَّذِينَ آمَنُوا مِنكُمْ وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ لَيَسْتَخْلِفَنَّهُم فِي الْأَرْضِ كَمَا اسْتَخْلَفَ الَّذِينَ مِن قَبْلِهِمْ وَلَيُمَكِّنَنَّ لَهُمْ دِينَهُمُ الَّذِي ارْتَضَى لَهُمْ وَلَيُبَدِّلَنَّهُم مِّن بَعْدِ خَوْفِهِمْ أَمْنًا يَعْبُدُونَنِي لَا يُشْرِكُونَ بِي شَيْئًا وَمَن كَفَرَ بَعْدَ ذَلِكَ فَأُوْلَئِكَ هُمُ الْفَاسِقُونَ﴾

"አላህ እነዚያን ከእናንተ ያመኑትንና መልካም ስራዎችን የሰሩትን እነዚያን ከእነሱ በፊት የነበሩትን እንደተካ በምድር ላይ በእርግጥ ኪተካቸው፤ ከእነሱም ያንን የወደደላቸውን ሃይማኖታቸውን ኪያደላድልላቸው፣ ከፍርሃታቸውም በኋላ ጸጥታን ኪለውጥላቸው ተስፋን ቃል ሰጥቷቸዋል። በእኔ ምንንም የሚያጋሩ ሆነው ይገዙኛል። ከዚያም በኋላ የካደ ሰው እነዚያ እነርሱ አመጸኞች ናቸው።" (ኑር: 55)

- **ተውሒድ የመልካም ፣ የደስታ ፣ የጣፋጭ ህይዎት ፣ የመረጋጋትን በሮች ይከፍታል።**

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿الَّذِينَ آمَنُواْ وَتَطْمَئِنُّ قُلُوبُهُم بِذِكْرِ اللهِ أَلاَ بِذِكْرِ اللهِ تَطْمَئِنُّ الْقُلُوبُ﴾

"(እነሱም) እነዚያ ያመኑ ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት የሚረኩ ናቸው። ንቁ! አላህን በማውሳት ልቦች ይረካሉ።" (አር'ረዕድ: 28)

﴿فَإِمَّا يَأْتِيَنَّكُم مِّنِّي هُدًى فَمَنِ اتَّبَعَ هُدَايَ فَلَا يَضِلُّ وَلَا يَشْقَى۞وَمَنْ أَعْرَضَ عَن ذِكْرِي فَإِنَّ لَهُ مَعِيشَةً ضَنكًا وَنَحْشُرُهُ يَوْمَ الْقِيَامَةِ أَعْمَى﴾

"ከእኔም የሆነ መሪ ቢመጣላችሁ መሪየን የተከተለ አይሳሳትም አይቸገርምም። "ከግሳጼዬም የዞረ ሰው ከእርሱ ጠባብ ኑሮ አለው። በትንሳኤም ቀን ዕውር ሆኖ እንቀሰቅሰዋለን።" *(ጣሃ: 123-124)*

በዚህ ታላቅ አጀንዳ እነዚህ ቀላል የሆኑ የተውሒድ አርማዎች ናቸው::

ባሳወቀን እንዲጠቅመን ፣ ለእኛ እንጅ በእኛ ላይ ማስረጃ እንዳይሆንብን እና ቀጥ ያለውን መንገድ እንዲመራን አላህን እማጸናለሁ::

والله أعلم

وصلى الله وسلم على عبده ورسوله نبينا محمد وآله وصحبه أجمعين

من معالم التوحيد

ከተውሒድ አርማዎች

إعداد: الشيخ عبدالرزاق بن عبدالمحسن البدر

ትርጉም፡ አቡ'ዓብዱልዓዚዝ/የሱፍ አሕመድ



ባህር ዳር በሚገኙ የአህለሱና መሻይኾች የተቀሩ ጠቃሚ ኪታቦች፣ ከሀገር ውስጥና ከውጭ በሚመጡ መሻይኾች የተሰጡ ኮርሶች፣ ሙሓዶራዎች፣ የጁመዓ ኹጥባ፣ በትክክለኛ ማስረጃ የተደገፉ የተለያዩ ኢስላማዊ መጣጥፎችን የሚከተለውን የቴሌግራም ኪንክ ጆይን በማድረግ መከታተል ይችላሉ

http://t.me/alateriqilhaq